# ህግህ ለእግሬ መብራት

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት - ዘዳግም

አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት



ክፍል አንድ

ከአድነው ተሾመ 1993 ዓ.ም

# ሕግህ ለእግሬ መብራት

ከአድነው ተሾመ

1993 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)

## ክፍል አንድ

ይህንን መጽሐፍ ያ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ
ወይም በከፊል ማባዛት ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው 1993 ዓ.ም

**Copyright 2001, Adnew Teshome**

# ምዕራፍ አራት

## ዘሌዋውያን

የኦሪት ዘሌዋውያን ማዕከላዊ መልዕክት፣ እስራኤላውያን ከአምላካቸው ጋር እንዴት ኅብረት ማድረግ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። «እኔ አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ»( ዘሌ 11፡44-45፣ 19፡2' 20፡7፣26) የሚለው ጥቅስ የመጽሐፉን አጠቃላይ ይዘት ያመለክታል። ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ቅዱስ ከሆነ አምላክ ጋር ኅብረት ለማድረግ በየጊዜው መቀደስ ስላለበት ኃጢአት በሠሩ ቁጥር ምን ለማድረግ እንዳለባቸው መመሪያን ይሰጣቸዋል። የኃጢአታቸውን መሥዋዕት የሚያቀርቡላቸውንና የሚያስተሰርዩላቸውንም ካህናት ያዘጋጅላቸዋል።

«ዘሌዋውያን» የሚለው ቃል ከአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች አንደኛው ከሆኑት ከ «ሌዋውያን»( የሌዊ ወገኖች) የመጣ ነው። እነዚህ የእስራኤል ካህናትና አገልጋዮች የነበሩ ወገኖች ናቸው። አገልግሎትን ከመስጠት ጋር የተያያዘ መጽሐፍም እንደሆነ ያመለክታል።

ይህንንም መጽሐፍ ሜኤ እንደጻፈ ይታመናል፡ ፡

ዘጸአት፡ - እግዚአብሔር ከሲና ተራራ በእሳትና በነጐድጓድ የተናገረበት መጽሐፍ ነው። - በሚያፈራ መንገድ።

ዘሌዋውያን ግን፡ - እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከመገናኛው ድንኳን ሆኖ የሚናገርበት መጽሐፍ ነው (ዘሌ. 1÷1-2) -በፍቅርና በምሕረት

በዘጸአት እስራኤላውያን በፋሲካ በግ ደም ነፃ ወጡ። ከኃጢአት ባርነት ነፃ የመውጣትና በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የመጽደቅ ምሳሌ ነው(Justification)።

«ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን» ለደኅንነት አንድ ጊዜ የሚሆን መታጠብ (ራእይ 1÷5)።

በዘሌዋውያን ውስጥ ግን መስዋዕት የሚያቀርቡት ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለመውጣት ሳይሆን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ከወጡ በኋላ ከቅዱስ አምላካቸው ጋር ኅብረት ለማድረግ ነው። ለቅድስና (Santification)።

1ኛ ዮሐ 1፡7 «ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።» ለቅድስና ሕይወት በየጊዜው

ሳያቋርጥ የምንነጻበት። ኅብረታችን ይቀጥል ዘንድ ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል።

በዘፍጥረት፡ - እግዚአብሔር ለሰው ውድቀት «ከሴቲቱ ዘር» መፍትሔን ሲያዘጋጅ እናያለን( ዘፍ. 3÷15)።

በዘጸአት፡ - እግዚአብሔር ለሰው ጩኸት በፋሲካ ደም ነጻነትን ሲያውጅ እናያለን።

በዘሌዋውያን ደግሞ ከመገናኛው ድንኳን በሚቀርቡት መሥዋዕቶች ለሰው መንፈሳዊ ረሃብ ከእርሱ ጋር ኅብረት የሚያደርጉበትን መንገድ ሲያዘጋጅ እናየለን።

## ዘሌዋውያን በሁለት አቢይ ክፍሎች ይከፈላል።

1. ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖራቸው ኅብረት መሠረት ስለሚሆኑ መሥዋዕቶች ዘሌ. 1-17
   .እግዚአብሔር በማቅርበት ሟዋዕቶች ይቅር እንደሚኚቸው
2. ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖራቸው ኅብረት የሚወስዷቸው ተግባራዊ የሆኑ ኃላፊነቶች ዘሌ 18-27

   - ምሕረትን ከተቀበሉ በኋላ በኃላፊነት መኖር እንዳለባቸው።

የመጀመሪያው ክፍል በአራት ይከፈላል ፡ -

1. ስለ መሥዋዕቶቹ (ምዕ. 1-7)
2. ስለ ካህናቱ (መሥዋዕቱን የሚያቀርቡ) (ምዕ.8-10)
3. ስለ ሕዝቡ (መሥዋዕቱን ስለሚያመጡ ሰዎች) መንጻት በነፍስም፣ በሥጋም (ምዕ. 11-16 )
4. ስለ መሠዊያው- በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለው ሌላ ቦታ መሠዋት አይቻልም (ምዕ. 17)።

ሁለተኛውም ክፍል በአራት ይከፈላል

1. ለሕዝቡ የተሰጡ መመሪያዎች (ምዕ. 18-20)
2. ለካህናቱ የተሰጡ መመሪያዎች (ምዕ. 21-22)
3. ስለ በዓላት የተሰጠ መመሪያዎች (ምዕ. 23-24)

4. ወደ ርስታቸው (ከነዓን ሲገቡ እንዲጠብቁት የተሰጣቸው መመሪያ (ምዕ. 25-27)

## ፩፥ የኅብረት መሠረት ስለሚሆኑ መሥዋዕቶች

### ከዘሌ 1-17

መሥዋዕቶቹ (ከምዕ. 1-7)

በዘሌዋውያን አምስት ዓይነት መሥዋዕቶች አሉ፡ -

1. የሚቃጠል መሥዋዕት ከእንስሳት (ምዕ. 1)
2. የእህል ቁርባን (ምዕ. 2)
3. የደኅንነት መሥዋዕት (ምዕ. 3)
4. የደኅንነት መሥዋዕት (ምዕ. 4
5. የበደል መሥዋዕት (ምዕ. 6፥7)
6. የመሥዋዕቶቹ አቀራረብና ሕግ (ምዕ. 6፥8-ምዕ. 7፥38)

የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእህል ቁርባንና፣ የደኅንነት መሥዋዕት፣ ለእግዚአብሔር የጣፋጭ ሽታ ሆነው በፈቃደኝነት ለምሥጋና ወይም ለስዕለት የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ናቸው።

የኃጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት፥ ሰዎች ኃጢአት ሲሠሩና ሲተላለፉ ማቅረብ ያለባቸው፤ ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ ያላቸው ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ፍርድ እንዳይገለጥ የሚከልሉ ወይም የሚሸፍኑ መሥዋዕቶች ናቸው።

- እግዚአብሔር የሚደሰተው ለኃጢአታችን በምናቀርበው መሥዋዕት ሳይሆን ከዚያ አልፈን በፈቃደኝነታችን በምናቀርበው የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት ነው።

ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ በመሆን የሚቀርቡት መሥዋዕቶች ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእግዚአብሔር አብ ጣፋጭ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡን የሚያሳዩ ሲሆኑ (ዕብ. 10፡5-10) የኃጢአትና የበደል መሥዋዕቶቹ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ኃጢአት ሲል የከፈለውን መሥዋዕትነት የሚያሳዩ ናቸው።

እግዚአብሔር አብ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» (ማቴ. 3፣17) ብሎ ሲናገር የኢየሱስ ሕይወት እንደሚቃጠል መሥዋዕት አብን ደስ እንዳሰኘ ያሳየናል።

የሚከተሉት ጥቅሶች ደግሞ ኢየሱስ የኃጢአት መሥዋዕት እንደሆነልን ያሳያሉ፤ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ.1፡ 29)፡፡ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት በመስቀሉ ላይ ተሸክሞ ስለነበረ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ» እስኪል ድረስ እግዚአብሔር አብ ከወልድ የራቀበት ጊዜ ነበር፡፡ «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ <u>ስለ ኃጢአታችን ሞተ</u>» (ሮሜ 5÷8)፡፡

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን <u>ስለ እኛ ኃጢአት</u> (<u>የኃጢአት መሥዋዕት</u>) አደረገው» (2ቆሮ. 5፡21)፡፡

## <u>የሚቃጠል መሥዋዕት</u> (ከእንስሳት ዘሌ.1)

ይህ መሥዋዕት ሁሉም <u>እንደ አቅሙ በፈቃደኝነት</u> ለእግዚአብሔር ጣፋጭ መሥዋዕት እንዲሆን የሚያቀርበው ነው፡፡

ሀ. ከላም መንጋ (በሬ) (ምዕ. 1፡3-9)
ለ. ከበጎች ወይም ከፍየሎች ተባቱን (ምዕ. 1፡10-13)
ሐ. ከዋኖስ ወይም ከርግብ (ምዕ. 1፡14-17)

ባለጸጋው፤ ከበሬ
መካከለኛው፤ ከበግ ወይም ከፍየል
ምንም የሌለው፤ ከዋኖስ ወይም ከርግብ ያቀርባል፡፡

- ሁሉም ግን የሚያቀርቡት «ነውር የሌለበትን» ነው (ዘሌ. 1፡3፣10)
- ሁሉም የሚያቀርቡትን (በሬም ሆነ በግ ወይም ፍየል ወይም ዋኖስ) እግዚአብሔር እንደ ጣፋጭ መስዋዕት በእኩልነት ይቀበለዋል (ዘሌ. 1፡9፣13፣17)

ይህ የሚቃጠል መስዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ራሱ ደም ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለአብ እንዳቀረበ ያሳስበናል፡፡

ይህ መስዋዕት ለእኛ ያለው ትርጉም፤ እኛም እንደ ጌታችን ራሳችንን መስዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔርና ለወንድሞቻችን መስጠት እንዳለብን ነው (ሮሜ 12÷1፤ 1ዮሐ. 3፡16)፡፡

## <u>የእህል ቁርባን</u> (<u>ዘሌ.2</u>)

ይህ ቁርባን ከመልካም ዱቄት የተዘጋጀ፣ ዘይት፥ ዕጣንና ጨው ያለበት መስዋዕት ነው:: ይህም መስዋዕት እንደ መጀመሪያው መስዋዕት ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በእሳቱ መሰዊያ ላይ የሚቃጠል የእህል ቁርባን ነው::

ይህ መስዋዕት የኢየሱስ ክርስቶስን ከኃጢአት ሁሉ ነጻ የሆነውን <u>ፍጹም የሰውነት ባሕሪውን</u> ያሳስበናል::

<u>መልካም ዱቄት</u>: - ፍጹም ባሕሪውን (ዕብ. 4፥15፤ 2፥15)

<u>ዘይት</u>: - በመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንደ ተቀባ (ሐዋ. 10፥38፤ ማቴ. 3፥16)

<u>ዕጣን</u>: - በሥጋው ወራት የጸለያቸውን ጸሎቶች ያሳስቡናል::

«እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር <u>ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ</u>» (ዕብ. 5፥7)::

<u>ጨው</u>: -<u>የጸጋ ምሳሌ</u> - «ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን» ቆላ. 4፥6::

በአንጻሩ ደግሞ ይህ መሥዋዕት <u>እርሾና ማር የሌለበት</u> ነበር::

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እርሾ የኃጢአት ምሳሌ እንደሆነ ተጠቅሷል (1ቆሮ. 5፥6-8፤ ገላ. 5፥9-10)::

በመሥዋዕቱ ውስጥ ማር አለመግባቱ ምን እንደሚያመለክት ባይታወቅም፥ ምናልባት፤ ማር በራሱ ጣፋጭ የሆነ ነገር ስለሆነ ለጣፋጭ ሽታ በሚቀርብ መሥዋዕት ውስጥ ቢገባ መሥዋዕቱን ያጣፈጠው ማሩ እንደሆነ እንዳይገመት ሊሆን ይችላል:: እኛም ማንኛውንም መሥዋዕት ስናቀርብ የራሳችንን የሥጋ ብልጠትና ጥበብ ጨምረንበት ጣፈጠልኝ ማለት እንደማንችል ያሳስበናል::

<u>ይህ መሥዋዕት ለእኛ ያለው ትምህርት</u>: -

ሀ. በባሕርያችን ክርስቶስን እንድንመስል
ለ. በመንፈስ ቅዱስ ዘይት (ቅባት) እንድንመላለስ
ሐ. ጸሎትንና ምልጃን እንድናቀርብ
መ. የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጎድለን::

## የደኅንነት (የሰላም) መሥዋዕት (ምዕ. 3)

መሥዋዕቱን አቅራቢው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዳለው የሚያመለክትበት መሥዋዕት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ሰላምን ለመመስረት መሥዋዕት እንደሆነልን የሚያመለክት መሥዋዕት ነው፡፡ በኢሳ.9፥6 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «የሰላም አለቃ» ብሎ ይጠራዋል፡፡ ኢሳ. 53፡5 ደግሞ «... የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ» ይለናል፡፡ እርሱ ለእኛ ደኅንነት ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅ ወይም ሰላም እንዲኖረን ሲል ያንን ሁሉ መከራ በመቀበል የደኅንነት መሥዋዕት ሆነልን፡፡

ኤፌ. 2፣14፣ እርሱ ሰላማችን ነውና... በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ..»

2ኛቆሮ. 5፡19 «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና...»

## የኃጢአት መሥዋዕት (ምዕ. 4)

ሰዎች ለሚሠሩት ኃጢአት የሚያቀርቡት መሥዋዕት ነው፡፡ ይህ መሥዋዕት የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት ሲል የኃጢአት መሥዋዕት እንደሆነልን ነው፡፡
2ቆሮ. 5፡21 «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት (የኃጢአት መሥዋዕት) አደረገው፡፡»

ይህ መሥዋዕት ከአዳም ከወረስነው የኃጢአት ተፈጥሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የሚያተኩረው ባለማወቅ (በተፈጥሮ ወይም በዘልማድ) ኃጢአት ላይ ነው፡፡«ማናቸውም ሰው ሳያውቅ ኃጢአት ቢሰራ...» (ቁ. 2)

ሌላ ከዚህ ምዕራፍ የምንረዳው ነገር፣ ለኃጢአታችን የምንከፍለው ዋጋ ወይም መሥዋዕት ከተሰጠን ኃላፊነት ጋር ተመጣጣኝ እንደሆነ ነው፡፡ የተቀባው ካህን፣ ወይም አንድ መኮንን፥ እንዲሁም አንድ ተራ ሰው ኃጢአት ቢሰሩ የሚያቀርበት የመሥዋዕት አይነት የተለያየ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

«<u>የተቀባውም ካህን</u> ... ኃጢአት ቢሰራ ስለሰራው ኃጢአት ነውር የሌለበት <u>ወይፈን</u> ለእግዚአብሔር ለኃጢአት መሥዋዕት ያቀርባል» ቁ. 3

«<u>አንድ መኮንንም</u> ሳያውቅ ኃጢአትን ሲሰራ ... ነውር የሌለበት <u>ተባት ፍየል</u> ለቁርባኑ ያቀርባል» ቁ. 22-23

«ከአገሩ ሕዝብም <u>አንድ ሰው</u> ኃጢአትን ሳያውቅ ቢሰራ... ለእርሱም የሰራው ኃጢአት ቢታወቀው ስለሠራው ኃጢአት ነውር የሌለባትን <u>እንስት ፍየል</u> ለቁርባኑ ያቀርባል» ቁ. 27-28

ካህኑ ከፍ ያለ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ስላለበት ስለ ኃጢአቱ ማቅረብ ያለበት አንድ ወይፈን ነው:: በኅብረተሰቡ ውስጥ ሥልጣን የተሰጠው አንድ መኮንን ደግሞ ኃጢአት ቢሠራ የሚያቀርበው አንድ ተባት ፍየል ነው:: አንድ ተራ እስራኤላዊ ኃጢአት ቢሠራ ግን የሚያቀርበው አንድ እንስት ፍየል ነው:: የሚያቀርባቸው መሥዋዕቶች ክብደት እየቀነሰ ሲመጣ እናያለን::

## <u>የበደል መሥዋዕት (ምዕ. 5÷1-ምዕ. 6÷7</u>)

ሆን ብሎ የተደረገ በደል (የእውቀት ኃጢአት) ላይ ያተኩራል:: ኃጢአት÷ ማንኛውንም መተላለፍና አመጽ የሚያመለክት ቃል ሲሆን፤ በደል ግን በዚያ በተደረገው ኃጢአት የተጎዳ (የተበደለ) ግለሰብ አለ ማለት ነው:: በደል በኃጢአት ውስጥ የተካተተ ቢሆንም ለየት ያለ ገጽታ አለው:: ለየት የሚያደርገውም በተደረገው ኃጢአት የተጎዳ (የተበደለ) ግለሰብ መኖሩ ነው::

ይህ መሥዋዕት በኃጢአት ምክንያት <u>ለተደረገው በደል</u> (✗☙☙❧⑤⑩❧) የሚደረግ መሥዋዕት ነው:: በሰዎችም ሆነ በእግዚአብሔር ላይ የተደረገን መተላለፍ የሚያስወግድ ነው (ምዕ. 6÷1-7)

ማንም በክርስቶስ ቢሆን <u>አዲስ ፍጥረት</u> ነው ተብሎ እንደተጻፈ፤ ኢየሱስ የኃጢአትን ተፈጥሮ (አዳማዊውን) ባህሪይ ከሻረ በኋላ፤ ሆን ብለንም ሆነ በዳተኝነት በየዕለቱ የምንፈጽመውንም ኃጢአት ሁሉ ይቅር ለማለት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ደሙን አፈሰሰልን::

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል» (1ኛ ዮሐ. 1÷7)::

በኤፌ. 2÷1 «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ» ሲል ከአዳማዊ ተፈጥሮአችን ስለወረስነው ኃጢአትና በተግባር ስላደረግነው በደል መናገሩ ነው፡፡

በዘሌ.5÷1 ላይ አንድ ሰው የሰማውንና ያየውን ነገር ለምስክርነት ሲጠየቅ ባይናገር ኃጢአት መስራቱ ነው ይላል፡፡ እኛም ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት የሰማነውን÷ ያየነውንና የቀመስነውን አለመመስከር ኃጢአት መሆኑን ያሳስበናል (1ኛ ዮሐ. 1÷1-2)

ከቁ. 2-13 «ማናቸውም ሰው ሳያውቀው ርኩስ ነገር ቢነካ...» በማለት አንድ ሰው ርኩስ በሆነ ነገር ቢረክስ ማቅረብ ያለበትን መሥዋዕት ይዘረዝራል፡፡

- ይህ መሥዋዕት ሁሉም አንደ አቅሙ ከጠቦት÷ ከዋኖስ ወይም ከመልካም ዱቄት የሚያቀርበው መሥዋዕት ነው ከእህል (ከመልካም ዱቄት) ከሆነ «የኃጢአት መሥዋዕት ነውና ዘይት አያፈስበትም፣ ዕጣንም አይጨምርበትም» ዘሌ. 5÷11 (ለጣፋጭ ሽታ አይደለምና)፡፡

ከቁ.14-19 ግን ማናቸውም ሰው ... ለእግዚአብሔር በተቀደሰው በማናቸውም ነገር ኃጢአትን ቢሰራ ... ነውር የሌለበትን አውራ በግ ያቀርባል ...»በማለት ለእግዚአብሔር በተቀደሰ ነገር ላይ ኃጢአትን መስራት የበለጠ ዋጋ እንደሚያስከፍል ያስተምረናል፡፡

ርኩስ በሆነ ነገር የረከሰ ሰው እንደ አቅሙ ከጠቦት ከዋኖስ ወይም ከመልካም ዱቄት መሥዋዕትን ሲያቀርብ ለእግዚአብሔር በተቀደሰው በማናቸውም ነገር ኃጢአትን የሰራ ግን አቅሙ ፈቀደም አልፈቀደም (ተበድሮም ቢሆን) ነውር የሌለበትን አውራ በግ ያቀርባል፡፡ አንድ ሰው ርኩስ በሆነ ነገር በረከስ ሲል በሥጋ ድካም የምናደርጋቸውን የሥጋ ኃጢአቶች ያመለክታል፡፡ ለእግዚአብሔር በተቀደሰው በማናቸውም ነገር ኃጢአትን በሰራ ሲል ግን ለእግዚአብሔር ክብር ለሆነ በሚገባው ነገር ላይ መተላለፍን ያመለክታል ይህ አይነቱ ኃጢአት በሥጋ ድካም ምክንያት ሚከሰስ ሳይሆን የአዋቂ አጥፊነትን የእግዚአብሔርን ክብር መጋፋትን የድፍረትና የትዕቢት ኃጢአት ያመለክታል

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለእግዚአብሔር በተቀደሰው ነገር ላይ ኃጢአትን ስለሰሩ ትልቅ ዋጋ ከከፈሉት በጥቂቱ፤

- ሙሴና አሮን፤ (ዘጸ.20÷7-13፤ ዘዳ.3÷23-26)
- የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ፤ (ዘሌ.10÷1-7)
- ሔሮድስ፤ (የሐዋ.12÷21-23)

ለእግዚአብሔር በተቀደሰው ነገር ላይ ኃጢአትን መስራት በተለይ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ሊጠነቀቁበት የሚገባ ነገር ነው::

<u>እነዚህ መሥዋዕቶች ለህይወታችን ያላቸው ትርጉም</u>

1. የበደል መሥዋዕት

በመጀመሪያ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣንበት ዋና ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአታችን (ስለ በደላችን) ስለወቀሰን ነው:: እነዚህም ኃጢአቶች <u>በተግባር የፈጸምናቸው በደሎች</u> ናቸው:: እግዚአብሔርንም ሰውንም እንደ በደልን ተረዳን:: ስለዚህ <u>የበደል መሥዋዕት</u> ወደ ሆነልን ወደ ኢየሱስ መጣን::

«እርሱም (መንፈስ ቅዱስ) መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል» (ዮሐ. 16÷8)::

«እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ 1፡29)::

2. የኃጢአት መሥዋዕት

የበደል መሥዋዕት ወደ ሆነልን ወደ ኢየሱስ ከመጣን በኋላ የዘላለምን ሕይወት እንዲሁም የበደላችንን ሥርየት ካገኘን በኋላ አሁንም በውስጣችን የሚዋጋን <u>የኃጢአት ተፈጥሮ</u> ስላለ ከኃጢአት ፍጹም ነፃ እንዳልሆንን ተረዳን::

1ዮሐ. 1፡8 «ኃጢአት የለብንም ብንል ውሸተኞች ነን::»

ሮሜ 7፡24 « እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ ለዚህ ሞት ከተሰጠው ሰውነት (የኃጢአት ተፈጥሮ) ማን ያድነኛል?»

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን ኢየሱስ ክርስቶስ የበደላችን መሥዋዕት ብቻ ሳይሆን <u>የኃጢአትም መሥዋዕት</u> እንደሆነ ተረዳን:: በውስጣችን

ባለው የኃጢአት ተፈጥሮ (ሥጋ) ላይ ድልን እንድናገኝ እርሱ መሥዋዕት ሆኖልናል። «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» (1ኛዮሐ. 1÷7)። ይህ ቃል የተጻፈው በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ለዳኑ ምዕመናን ነው።

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና። ከሥጋ ከአዳማዊ የኃጢአትም ተፈጥሮ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ አርነት አውጥቶኛልና። ከሥጋ (ከአዳማዊው የኃጢአት ተፈጥሮ) የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎልና (አስችሎናልና)፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ <u>ኃጢአትን</u> በሥጋ ኰነነ» (ሮሜ 8÷1-3)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ኃጢአት እንዳይገዛን የመንፈስን ኃይል ሰጠን።

## 3. ክርስቶስ የሰላም መሥዋዕት ሆነልን፤

ክርስቶስ ኢየሱስ የበደላችንም (የተግባር ኃጢአት) ሆነ የኃጢአታችን (የኃጢአት ተፈጥሮ) መሥዋዕት መሆኑን ከተረዳን በኋላ ከኃጢአት ውጤት (የዘላለም ሞት፡ - ሮሜ 6፡23) ብቻ ሳይሆን ከኃጢአትም ኃይል (ከሕግ፡ -1ቆሮ. 15፡56) ነጻ ሆነን የሚቀጥለውን <u>የደኅንነት (የሰላም) መሥዋዕት ለመቀበል</u> ቻልን።

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላም መሥዋዕት ሆኖ ራሱን እንዳቀረበልን ተረድተን ከእግዚአብሔር፣ ከሰዎችና ከራሳችንም ጋር አእምሮን በሚያልፍ ሰላም መኖር ቻልን። ከሕግ ቀንበር ነጻ ያልሆነ ክርስቲያን የኢየሱስን የሰላም መሥዋዕትነት ሊቀበል አይችልም። ምክንያቱም ለእርሱ እግዚአብሔር «ይህን አድርግ፤ ያንን አታድርግ» የሚል አምላክ ብቻ እንጂ ያንን ሕግ የምንኖርበትንና የምናሸንፍበትን መንፈሳዊ መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት በኩል እንዳዘጋጀልን ገና አልተረዳም፤ ስለዚህ ሊኖርበት አይችልም።

«ሰላሜ በዝቶልኝ እንዲህ የምኖረው፤
ወዶኝ በሞተልኝ በጌታ የሱስ ነው።» ብሎ መዘመር የሚችል÷ ኢየሱስ ክርስቶስ የበደል መሥዋዕት (ስለመተላለፋችን) የኃጢአት መሥዋዕት (ከአዳም ለወረስነው የኃጢአት ተፈጥሮ) እንዲሁም የሰላም መሥዋዕት እንደሆነለት የተረዳና የሚኖርበትም ክርስቲያን ብቻ ነው።

ፊል 4፣6-7 «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።»

- ኢየሱስ፤ የሰላም መስዋዕት ሆኖልን፥ ከእግዚአብሔር፥ ከሰዎችና ከራሳችን ጋር አስታርቆናል። «እርሱ ሰላማችን ነውና» (ኤፌ. 2፥14)። ከስሞቹም አንዱ «የሰላም አለቃ» ነው (ኢሳ. 9፥6)።

## 4. የእህል ቁርባን ምሳሌ ሆነልን

የክርስቶስን ባህርይ መምሰል፤

በኃጢአት ውጤትና በኃጢአት ኃይል ላይ ድልን ካገኘንና በሰላም መኖር ከጀመርን በኋላ ሕይወታችንና ባህርያችን <u>በእህል ቁርባን</u> የሚመሰለውን <u>የክርስቶስን ባህርይ እየመሰለ ይመጣል</u>። የእህል ቁርባን ከመልካም ዱቄት እንደሚቀርብ የእኛም ሕይወት መልካም የሆነውን የኢየሱስን ባህርይ ይመስላል።

(ሮሜ 8፡29) «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና።

## 5. የሚቃጠል መሥዋዕት

ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰልን በምንሄድበት ጊዜ ሕይወታችን እንደሚቃጠል መስዋዕት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል። ኢየሱስ ራሱን እንደሚቃጠል መሥዋዕት ለአባቱ እንዳቀረበ እኛም ህይወታችንን እንደሚቃጠል መስዋዕት አድርገን መኖር እንጀምራለን። ሙሉ ለሙሉ በተሰጠ ሕይወት ራሳችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ወደ ማቅረብ እንደርሳለን (ሮሜ 12፥1-2)

ጳውሎስ ህይወቱ የዚህን ዓይነት (የሚቃጠል) መስዋዕት ሊሆን ፈቃደኛ እንደነበረ ይገልጻል። «ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና አገልግሎት ተጨምሬ ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ ደስ ብሎኛል» (ፊል. 2፥17)። በመጨረሻም፣ በዚሁ ዓይነት መሥዋዕትነት እንደሚሞት ይናገራል። «በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል» (1ኛ ጢሞ. 4፥6)።

«... እኛም ስለወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል» (1ዮሐ. 3÷16)።

ካህናቱ -( -ዘሌ. ምዕ. 8፣9እና 10)

ሀ. በምዕ. 8 - ካህናቱ (አሮንና ልጆቹ) ሲቀደሱ እናያለን።
ለ. በምዕ. 9 - ካህናቱ አገልግሎት ሲጀምሩ እናያለን።
ሐ. በምዕ.10 - ካህናቱ (ናዳብና አብዩድ) ሲቀጡ (ሲቀሰፉ) እናያለን።

ሀ. ካህናቱ ሲቀደሱ- ምዕራፍ 8

1. ሙሴ፤ አሮንንና ልጆቹን በውኃ አጠባቸው (ቁ. 6) ውኃ የቃሉ ምሳሌ ነው።
2. የክህነት ልብሳቸውን አለበሳቸው (ቁ. 7 እና 13)። በክርስቶስ ያገኘነውን ጽድቅ ያመለክታል።
3. አሮንን (ሊቀ ካህኑን) በቅብዓቱ ዘይት ራሱን ቀባው (ቁ. 12)። የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ያመለክታል።
4. ለኃጢአታቸው የሚሆን የኃጢአት መሥዋዕት ወይፈን አቀረበላቸው (ቁ. 14-17)።
5. ለጣፋጭ ሽታ የሚሆን የሚቃጠል መሥዋዕት አውራ በግ አቀረበ (ቁ. 18-21)
6. ለቅድስና መሥዋዕት የሚሆን ሁለተኛ አውራ በግ አቀረበ። ቁ.(22-29)። ይህ የቅድስና መሥዋዕት ከምዕራፍ 1-5 ከተዘረዘሩት አምስት መሥዋዕቶች የተለየ፣ ካህናት ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚለዩበት (የሚቀደሱበት) መሥዋዕት ነበረ።

የክህነታቸው ሥነ ሥርዓት ሰባት ቀናት ነበረ የወሰደው(ቁ. 33-36)።

አሮን (ሊቀ ካህኑ) የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።

የአሮን ልጆች (ካህናቱ) ደግሞ የአዲስ ኪዳን አማኞች ምሳሌ ናቸው።
«እናንተ ግን... የንጉሥ ካህናት... ናችሁ» (1ኛጴጥ. 2÷9)።
«ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ»( ራእይ 1÷6)።

ሙሴም ከቅድስናው መሥዋዕት ደም ወስዶ አሮንንና ልጆቹን፡ -

- ቀኝ ጆሮአቸውን
- የቀኝ እጃቸውን አውራ ጣት

- የቀኝ እግራቸውን አውራ ጣት በደም ሲቀድስ እናያለን።

የዚህ ትርጉም

- በጆሮአቸው- የእግዚአብሔርን ሰማያዊ መመሪያ እንዲያዳምጡ
- በእጃቸው የእግዚአብሔርን ሥራ በትጋት እንዲሠሩ
- በእግራቸው በእግዚአብሔር መቅደስ በቅድስና እንዲመላለሱ ነው።

ለክህነት አገልግሎት በሚቀደሱበት ጊዜ ለሰባት ቀናት (የክህነታቸው ሥርዓት እስኪፈጸም) ከመገናኛው ድንኳን እንዳይወጡ ያስጠነቅቃቸዋል። ከወጡ እንደሚሞቱ ይነግራቸዋል።

በቁ. 35 «የእግዚአብሔርን ሥርዓት ጠብቁ በማለት ያስጠ ነቅቃቸዋል። እነርሱ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ካልጠበቁ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት እንዲጠብቅ ማድረግ እንዴት ይችላሉ?

## ለ. <u>ካህናቱ አገልግሎት ሲጀምሩ- ምዕራፍ 9</u>

- ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ አገልግሎት የሚመጣው በመጀመሪያ <u>ከተገለገልን</u> (ከተቀደስን) በኋላ እንደሆነ ነው። በምዕ. 8 ተገለገሉ (ተቀደሱ) በምዕ. 9 ማገልገል ጀመሩ (ቀደሱ)።
- ሰባት ቀናት ከተቀደሱ በኋላ በስምንተኛ ቀን ማገልገል ጀመሩ። በምዕ. 8 ሙሴ ለአሮንና ለልጆቹ ያቀረበውን መሥዋዕት በምዕ. 9 አሮን ለሕዝቡ ሲያቀርብ እናያለን (ቁ. 1-7)።
- «ሙሴም አሮንን: - ወደ መሠዊያው ቀርበህ የኃጢአትህን መሥዋዕትና የሚቃጠለውን መሥዋዕትህን ሠዋ ለራስህና ለሕዝቡም አስተሰርይ...» ይለዋል (ቁ. 7)።

<u>የቀረቡት መሥዋዕቶች፤</u>

- የኃጢአት መሥዋዕት ቁ. (8-11 እና ቁ. 15)
- የሚቃጠል መሥዋዕት፤ ቁ (12-14 እና ቁ.( 16)
- የደኅንነት መሥዋዕት ቁ. (18-21) ነበሩ።

<u>መሥዋዕቶቹን ሁሉ ከሰዋ በኋላ፤</u>
«አሮን እጆቹን ወደ ሕዝቡ ዘረጋ <u>ባረካቸውም</u>» (ቁ. 22)

«ሙሴና አሮንም ወደ መገናኛው ድንኳን ገቡ ወጡም ሕዝቡንም ባረኩ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ለሕዝቡ ሁሉ ተገለጠ» (ቁ. 23)።

- እውነተኛ ባርኮት የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጣል። «እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጣ በመሠዊያው ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ስቡንም በላ ሕዝቡም ሁሉ አይተው እልል አሉ፤ በግምባራቸውም ወደቁ» (ቁ. 24)።

## ሐ. ካህናቱ (ናዳብና አብዩድ) ሲቀሰፉ - ምዕራፍ 10

በዚህ ምዕራፍ በጣም የሚያሳዝን ነገር እናነባለን። ናዳብና አብዩድ (የአሮን ልጆች) እግዚአብሔር ያላዘዘቸውን ሌላ እሳት በጥናው ውስጥ አድርገው ሲያጥኑ እናያለን። ይህንን በማድረጋቸው እሳት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ በላቸውና በእግዚአብሔር ፊት ሞቱ (ቁ. 1-2)።

በምዕ. 9 ላይ የእግዚአብሔር እሳት ከእግዚአብሐር ዘንድ ወጥቶ በመሠዊያው ላይ የነበረውን መሥዋዕት እንደበላና ሕዝቡን ሁሉ እልል እንዳስባለ ስናይ፤ በምዕ. 10 ላይ ደግሞ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ የተቀቡት ካህናት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላቃለሉ ያው የእግዚአብሔር እሳት ሲበላቸው እናያለን። ሙሴም አሮንን፡ -( ቁ. 3) «*በፊቴ ቀርቦ የሚያገለግለኝ ሁሉ ቅድስናዬን ያክብር* እኔም በሕዝቤ ፊት የተከበርሁ እሆናለሁ እያለ በተናገረበት ጊዜ ይህንን ማስጠንቀቁ ነበር እኮ» ይለዋል (በ1980 እትም)። ቀጥሎም ሙሴ ለአሮንና ለቀሩት ለሁለቱ ልጆቹ (ቁ. 6) «ራሳችሁን አትንጩ ልብሳችሁንም አትቅደዱ» በማለት ያስጠነቅቃቸዋል። በአዲስ ኪዳንም «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነው» (ዕብ. 12÷29) የሚል ማስጠንቀቂያ አለ።

### በዚህ ክፍል (ከቁ. 1-7) የምንማረው

1. እግዚአብሔር በሚሰጠን ጸጋ፣ ኃይልና ምሪት እንጂ በራሳችን ፊቃድና ኃይል ወይም መንገድ እግዚአብሔርን ማምለክም ሆነ ማገልገል እንደማንችል ነው። «... የሚያገለግልም እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል» (1ኛ ጴጥ. 4÷11)። ትምክህት ስንጨምርበት ወይም በራሳችን ኃይል ሲመስለን የእግዚአብሔርን ቁጣ በራሳችን ላይ እንጠራለን። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» የሚለን። «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነው»

የሚለው ቃል ብሉይ ኪዳን ወስጥ ሳይሆን አዲስ ኪዳን ወስጥ መሆኑን ደግመን ማስተዋል አለብን፡፡

2. እግዚአብሔር በሚያደርገው ሁሉ ጻድቅ ስለሆነ የእግዚአብሔር ካህናት ከሆንን እግዚአብሔር ባደረገው ነገር ላይ ማጉረርና እግዚአብሔርን መክሰስ አንችልም፤ የክህነት ልብሳችንን (ፈሪሃ እግዚአብሔርን) መቅደድ አልተፈቀደልንም፡፡ የባሰ ነገር (ቅጣት) እንዳይመጣ፡፡
   ሙሴም፤ «<u>እንዳትሞቱ፣</u> <u>በማኅበሩም ላይ ቁጣ እንዳይወርድ</u> ራሳችሁን አትንጩ፣ ልብሳችሁንም አትቅደዱ ብሎ አስጠነቀቃቸው (ቁ 6)፡፡

## *<u>ስለ ሕዝቡ</u>* -- (ከዘሌ. 11-16)

1. <u>በመብል መቀደስ</u> (ምዕ. 11)

ከእንስሳት መካከል የትኞዎቹ እንደሚበሉና እንደማይበሉ ይነግራቸዋል፡፡ «የተሰነጠቀ ሰኮና ያለውንና የሚያመሰኳውን እንስሳ ሁሉ ብሉ... በእናንተ ዘንድ ርኩሶች ናቸው»( ዘሌ. 11÷3-8)፡፡ በአዲስ ኪዳን ስለ መብል ጉዳዩ የሚናገረውን በምናይበት ጊዜ ከብሉይ ኪዳን የተለየ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

- ኢየሱስ ሕዝቡን ጠርቶ፤ «ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባው አይደለም፣ ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው አላቸው» (ማቴ. 15÷11)፡፡
- ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መብል ሲናገር እንዲህ ይላል፤ «በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ፣ ተረድቼአለሁም፤ ነገር ግን ማንም ርኩስ እንዲሆን ለሚቆጥር ለእርሱ ርኩስ ነው ... ሁሉ ንጹህ ነው በመጠራጠር የተበላ እንደሆነ ግን ለዚያ ሰው ክፉ ነው»(ሮሜ 14÷14፤20)፡፡ እንደሁም ለጢሞቴዎስ እንዲህ ይለዋል፤ «<u>እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና</u> ከምስጋና ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና» ( 1ኛጢሞ. 4÷4-5)፡፡
- በመብል ምክንያት ማንም በማንም ላይ መፍረድ እንደሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ያስጠነቅቀናል (ሮሜ 14÷1-4 6÷10፤ ቆላ.2÷ 16-17)፡፡

■ ታዲያ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ከሆነ በብሉይ ኪዳን ይህንን ብሉ ይህንን አትብሉ የሚላቸው ለምንድነው? በአጠቃላይ ዘሌዋውያንን በምንመለከትበት ጊዜ የእግዚአብሔር ዓላማ የእስራኤል ሕዝብ ከሌሎች አሕዛብ ተለይቶ ለእርሱ የተቀደሰ እንዲሆኑ ነበረ። ይህንንም ሊያደርግ የወደደበት አንዱ መንገድ በሚበሉት የእንስሳት አይነት ነበረ። አዳምና ሔዋንን «ከዚህች ፍሬ አትብሉ» ብሎ ያዘዛቸው በፍሬው ውስጥ የሚገድል መርዝ ስለነበረ ሳይሆን ለእርሱ ያላቸውን ታዛዥነት መመዘኛ እንዲሆን ነበረ። የሞቱትም ፍሬው መርዝ /food poison/ ሆኖባቸው ሳይሆን፣ ፍሬውን በመብላታቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለተላለፉ ነው፡፡ በዘሌዋውያንም እግዚአብሔርን ለእስራኤላውያን ያላቸው «እነዚህ እንስሳት በራሳቸው ርኩሳን ስለሆኑ አትብሏቸው» ሳይሆን «በእናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸው» ነው ያላቸው፡፡ በዘሌዋውያን ምዕራፍ አስራ አንድ «በእናንተ ዘንድ» የሚለው ሐረግ 17 ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ ስለ መብል የተሰጣቸው ትእዛዝ « በእነርሱ ዘንድ» እና« በእነርሱ ዘመን» እንደነበረ ያሚከታል፡፡ ለእነርሱ ዘመን (ለብሉይ ኪዳን ዘመን )ብቻ እንደነበረ የሚያረጋግጡልን ከላይ የጠቀስናቸው የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ናቸው።እነዚያ እንስሳት በእውነት ርኩሳን ቢሆኑ ኖሮ÷ በአዲስ ኪዳን «እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነው» ባላለም ነበረ። በዚያ በብሉይ ኪዳን ዘመን «በእናንተ ዘንድ» ብሎ የሰጣቸው ትእዛዝ ነበረ።

2. በመውለድ ጊዜ መቀደስ (መንጻት)

ዘሌ. 12፡ - ሴት ስትወልድ እንዴት እንደምትነጻ፤
በተለይ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት፣ ወንድ በአርባ ቀን ሴት ደግሞ በሰማኒያ ቀን ትጠመቅ የሚል ባህል የመጣው ከዚህ ምዕራፍ ነው። ነገር ግን ምዕራፉ በሙሉ የሚናገረው ስለ እናትየዋ መንጻት እንጂ ስለ ልጆቹ አይደለም። «... መስዋዕት ታቃርባለች፣ ካህኑም ያስተሰርይላታል፤ እርስዋው (እናትየዋ) ትነጻለች» (ቁ. 8)።

በሉቃስ 3÷22-24 ቅድስት ማርያም ይህንን ትእዛዝ እንደፈጸመች እናነባለን። በዚያን ዕለት ሕጻኑን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ቤተመቅደስ የወሰደችው ግን በዘጸአት 13÷2 «ማሕጸንን የሚከፍት በኵርን ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ» ብሎ እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት ስለነበረ ነው እንጂ ሌላ ሥርአት ሊደረግለት አልነበረም። የተጠመቀው በ30 አመቱ እንደነበረ በሉቃስ 3÷21-23 እናነባለን።

3. <u>በሰውነት ሁሉ መቀደስ (መንጻት)</u>

ዘሌ. 13፡1-46- *ስለ ለምጽ ደዌ የተሰጠ ሕግ*

- ስለ ልዩ ልዩ የቆዳ በሽታዎችም ይናገራል። በብሉይ ኪዳን፣ ለምጽ የኃጢአት (የርኩሰት) ምሳሌ ሲሆን የእግዚአብሐርን ቅጣትም ያመለክታል (ዘኍ. 12፥10፤ 2ነገ. 5፥27፤ 2ዜና 26፥16-21)።

«ደዌውም ወደ ሥጋው ቁርበት ቢጠልቅ እርሱ የለምጽ ደዌ ነው፤ ካህኑም አይቶ፣ ርኩስ ነው ይበለው» (ዘሌ. 13፥3)። ኃጢአት በነፍሳችን ጠልቆ እንዲገባ መፍቀድ የለብንም። ኃጢአታችንን ቶሎ ቶሎ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መታጠብ አለብን።

«የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ልብሱ የተቀደደ ይሁን... ርኩሱም እርኩስ ነኝ ይበል። ደዌው ባለበት ዘመን ሁሉ ርኩስ ይሆናል... መኖሪያውም ከሰፈር ውጭ ይሆናል» (ዘሌ. 13፥45-46)። ኃጢአት (ለምጽ) ሰውን እንደሚያጎሳቁልና ከኅብረት እንደሚለይ የሚያመለክት ቃል ነው። ኃጢአት በሕይወታችን እስካለ ድረስ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ኅብረት ሊኖረን አይችልም( ኢሳ. 59፥1፤ 1ዮሐ. 1፥5-7)። ኃጢአት ከሕይወታችን እንዲወገድ በንሥሐና በጸጸት በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ አለብን (ያዕ. 4፥8-10፤ 1ዮሐ. 1፥7-9)።

4. <u>በልብስ መቀደስ መንጻት</u>

ዘሌ. 13፡47-59፤ የልብስ ከርኩሰት ነጻ መሆን የቅዱሳን ልብስ የጽድቅ ሥራ ነው (ራእይ 19፥8)፤ የሚነጻውም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው (ራእይ 7፥13-14)። «ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ» (ራእይ 3፥4)።

5. <u>የለምጻም ሰው የመንጻት ሕግ</u>፡ -(ዘሌ 14፡1-32)

አንድ ለምጻም ሰው ከለምጹ በሚነጻበት ቀን የሚከናወኑ ሥርዓቶች፡ -

ሀ. ካህኑ ሁለት ንጹህ ወፎች ይወስዳል። አንዱ ወፍ ከታረደ በኋላ በታረደው ወፍ ደም ውስጥ ሕያውን ወፍ፣ የዝግባ እንጨት፤ ቀይ ግምጃና ሂሶጵ ወስዶ ይነክራቸውና ከለምጽ በሚነጻው ሰው ላይ <u>ሰባት ጊዜ ይረጫል</u>። ለምጻሙም ሰው ንጹህ ይሆናል( ዘሌ 14፡1-7)።

በደም መረጨት ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ እንደዋጀን ያመለክታል /Redemption/ እኛም ከኃጢአታችን ለምጽ የነጻነው በክርስቶስ ደም ተረጭተን ነው (ዕብ. 10፡21-22)።

ለ. ከለምጽ የነጻው ሰው ልብሱን ያጥባል፣ ጠጉሩን ይላጫል በውኃም ይታጠባል፣ ንጹህም ይሆናል (ዘሌ 14፥8)።

- ውኃ የቃሉ ምሳሌ ነው። «እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ»( ዮሐ. 15፥3)።

በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ » (ኤፌ. 5፥26) ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ውሃ አጠበን /Santification/ ፡ ፡

ሐ. ካህኑ የበደል መሥዋዕት ያቀርብና ከደሙ ወስዶ ከለምጽ የነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፣ የቀኝ እጁንም አውራጣት፣ የቀኝ እግሩንም አውራ ጣት ያስነካዋል( ዘሌ. 14፡12-14)።

ይህ፥ ከኃጢአታችን ለመዋጀት የምንረጨው ሳይሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከዕለታዊ ኃጢአታችን የምንነጻበት ነው /Santicfication/ (ዕብ. 9፡13-14)።

መ. ካህኑ ዘይት ወስደ ደም የነካውን ቀኝ ጆሮ፣ የቀኝ እጅ አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን አውራ ጣት በዘይቱ ያስነካዋል። የተረፈውንም ዘይት በሚነፃው ሰው ራስ ላይ ያፈስበታል ( ዘሌ. 14፡15-18)። ዘይት በመንፈስ ቅዱስ የመቀባት ምሳሌ ነው። (Anointhing)

ሠ. የኃጢአት መሥዋዕት ያቀርባል (ዘሌ 14፡19)።

ረ. የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህሉን ቁርባን ያቀርባል ለእግዚአብሔር መልካም መዓዛና ሽታ ያለው መስዋዕት( ዘሌ. 14፡20)።

ደሙ፣ ውኃውና መንፈሱ (ቅባቱ)፡ – «የሚመሰክሩት መንፈሱና፣ ውኃው፣ ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ» (1ኛ ዮሐ. 5፥8)።

በዚህ ምዕራፍ ከለምጽ የሚነጻው ሰው የሚነጻበት ሥርአትና በምዕራፍ ስምንት ላይ ካህናቱ የተቀደሱበት ሥርዓት ብዙ ተመሳሳይነት አለው። ይህ የሚያሳየን ካህንም ሆነ ተራ ለምጻም ሰው ሁለቱም ኃጢአተኞች እንደሆኑና ደሙ፣ ውኃውና መንፈሱ (ቅባቱ) እኩል እንደሚያስፈልጋቸው ነው (ሮሜ 3፥23፤ ሐዋ. 2፥17)።

6. <u>የቤት መቀደስ</u> (ዘሌ 14፡33-53)

በቤት ውስጥ ደዌ ሲኖር ቤቱ የሚነጻበትን ሥርዓት ይዘረዝራል፡፡ በ1ኛ ጴጥ. 2÷5 የአዲስ ኪዳን አማኞች፤ «እናንተ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤት ናችሁ» ስለተባልን ለእኛ የሚሆን ትምህርት ከዚህ ክፍል ማግኘት እንችላለን፡፡
ደዌ፡ - የኃጢአት ምሳሌ ነው
ካህናችን፡ - ኢየሱስ ክርስቶስ ነው
የሚረጨው ደም፡ - የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምሳሌ ነው፡፡

- ይህ ክፍል ለግል አማኝ ብቻ ሳይሆን በትዳር ለተጣመሩና ቤተሰብን ለመሠረቱ የክርስቲያን ቤተሰቦችም ትምህርት አለው፡፡

ቁ. 34 «የለምጽ ደዌ በርስታችሁ ምድር በአንድ ቤት ባደረግሁ ጊዜ» ኃጢአት በቤት ውስጥ ሲገባ፡ - እግዚአብሔር ያለ ምክንያት የለምጽን ደዌ በአንድ ቤት አያደርግም፡፡ – በብሉይ ኪዳን ለምጽ የርኩሰትና የእግዚአብሔር ተግሣጽ ምልክት ነው፡፡
ቁ. 35 «ባለቤቱ መጥቶ ካህኑን፡ - ደዌ በቤቴ ውስጥ ያለ ይመስለኛል ብሎ ይንገረው፡፡» የቤቱ ባለቤት ለካህኑ መንገር አለበት ፡ - እኛም ኃጢአት በሕይወታችን (በቤታችን) ያለ ሲመስለን ወደ ሊቀ ካህናችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጉዳዩን ማቅረብ አለብን፡፡
ቁ. 36 «ካህኑም በቤቱ ወስጥ ያለው ዕቃ ሁሉ እንዳይረክስ... <u>ቤቱን ባዶ</u> እንዲያደርጉት ያዝዛል በኋላ ካህኑ ቤቱን ለማየት ይገባል፡፡»

- ደዌው ችላ ከተባለ ወደ ሌሎች ዕቃዎች ስለሚዛመት የቤቱን ዕቃ ሁሉ ወደ ውጭ ያስወጣል፡፡ እኛም ጌታን ወደ ቤታችንና ወደ ጓዳችን ስንጋብዘው <u>ባዶ ሆነን</u> በፊቱ ለመቅረብ ፈቃደኛ መሆን አለብን፡፡ ከእኛ ቅራቅንቦ ጋር እየተጋፋ በቤት ውስጥ አይመላለስም፡፡
- ቁ. 37 «ደዌውንም ያያል...»

ካህኑ የደዌውን ዓይነትና ጥልቀት ይመረምራል፡፡ እኛም ጌታ የሕይወታችንንና የቤታችንን ደዌ እንዲመረምር እንፍቀድለት፡፡
ቁ. 38-39 «... ሰባት ቀን ቤቱን ይዘጋዋል፡፡ ካህኑም በሰባተኛው ቀን ተመልሶ ያያል ...» በሕይወታችንና በቤታችን ያለ ችግር ሁሉ በቅጽበት አይፈወስም፡፡ የእግዚአብሔርን ተግሣጽና ቅጣት መታገስ አለብን፡፡ የሚያስፈልገውን ያህል ጊዜ መውሰድ አለብን፡፡ ካህኑ (ኢየሱስ )ተመልሶ እንዲያየው ማድረግ አለብን፡፡

ቁ. 40-42 «ደዌ ያለባቸውን ድንጋዮች እንዲያወጡና ከከተማ ውጭ ወደ ረከሰው ስፍራ እንዲጥሉአቸው ያዝዛል። ቤቱንም በውስጡ በዙሪያውም ያስፍቀዋል፤ የፋቁትንም የምርጊቱን አፈር ከከተማው ወደ ውጭ ወደ ረከሰ ስፍራ ያፈስሱታል። በእነዚያም ድንጋዮች ስፍራ ሌሎች ድንጋዮች ያገባሉ፤ ሌላም ጭቃ ወስደው ቤቱን ይመርጉታል።» ሊቀ ካህናችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወታችንና በቤታችን ቀዶ ጥገና እንዲያደርግ እንፍቀድለት። ካንሰር የሆነብንን ነገር አውጥቶ ይጥላል፤ መልካም በሆነ ነገርም ይተካዋል።

ሀ. ደዌ ያለባቸው ድንጋዮች ወጥተው ወደ ውጭ ይጣላሉ።

- በሕይወታችን የረከሰውን ነገር፡ -(በአስተሳሰብ፣ በአነጋገር፣ በድርጊት ቢሆን )አውጥተን ወደ ውጭ (ደግመን በማናገኘው ሥፍራ) መጣል አለብን።
- «አሮጌውን ሰው አስወግዱ» ኤፌ. 4፡23

ለ. ቤቱ ይፋቃል፡ - የዚያ ነገር ትዝታ ሁሉ እንዲጠፋ። «በአእምሮአችሁ መንፈስ ታደሱ» ኤፌ. 4፡23

ሐ. ሌሎች (ጤናማ) ድንጋዮች በስፍራው ይገባሉ። በኃጢአት በተሰናከልንባቸው ነገሮች ፈንታ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ነገር እንተካለን።

«... አዲሱን ሰው ልበሱ »(ኤፌ. 4፡24)

ቁ. 49-53- የወፍ ደም ፈስሶ ካህኑ <u>ለቤቱ ያስተሰርይለታል</u>።

- የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የቤትን (የቤተሰብን፣ የትዳርን) ኃጢአትና ደዌ ሁሉ ያነጻል።

7. ከሰውነቱ ፈሳሽ ነገር ለሚወጣ ሰው የመንጻት ሥርዓት (ምዕ. 15) (የሰውነት መንጻት)

- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ <u>14 ጊዜ</u> «በውኃ ይታጠብ» ይላል። ውኃ የቃሉ ምሳሌ ነው።

8. የእስራኤላውያን የሥርየት ዕለት (<u>የማስተሰሪያ ቀን</u>) (ምዕ. 16)

- በዚህ ምዕራፍ ሊቀካህኑ፤
- ለራሱና ለቤተሰቡ (ቁ. 11)
- ለሕዝቡ (ቁ. 15)
- ለመቅደሱና ለመገናኛው ድንኳን (ቁ. 16)
- ለመሠዊያው (ቁ. 18-19)

- ለቅድስተ ቅዱሳኑ (ቁ. 33)

በዓመት አንድ ቀን የሚያስተሰርይበት የሥርየት ቀን ነው፡፡
<u>የኃጢአት መሥዋዕት</u> ካቀረበ በኋላ
የሚቃጠል መሥዋዕት ለራሱና ለሕዝቡ ያቀርባል ቁ. 24

- የኃጢአት መሥዋዕት፡ - «ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ» ማለት ነው፡፡
- የሚቃጠል መሥዋዕት፡ - «ጌታ ሆይ አመሰግንሃለሁ፣ አመልክሃለሁ» ማለት ነው፡፡

የኃጢአት መሥዋዕት ሳይቀርብ የሚቃጠል መሥዋዕት አይቀርብም፡፡ እስከነ ኃጢአታችን ለእግዚአብሔር የምሥጋና ወይም የአምልኮ መሥዋዕት ማቅረብ አንችልም፡፡ በመጀመሪያ የኃጢአት መሥዋዕት÷ ማለትም የንሥሐ ጸሎት ማድረግ አለብን፡፡
መቅደሱ፣ የመገናኛው ድንኳን፣ መሠዊያውና ቅድስተ ቅዱሳኑ የኃጢአት ማስተሰርያ ቦታና ዕቃ ናቸው፤ ነገር ግን እነርሱ እንኳን በእስራኤላውያን ኃጢአትና ርኩሰት እንዳይረክሱ በዚህ ዕለት (በማስተሰሪያ ዕለት) ካህኑ ለእነርሱም ያስተሰርይላቸዋል፡፡

- ቆሻሻን እጅ የሚያነጻው ሳሙና እራሱ ደግሞ በእጁ ላይ በነበረው ቆሻሻ ሊቆሽሽ ስለሚችል ሳሙናውም መታጠብ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ ማለት ነው፡፡
- ሳሙናውን ለማንጻት ብንጠቀምበትም ራሱንም ማንጻት ይኖርብናል፡፡ በግል ሕይወታችንም ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ (ለእግዚአብሔር ለመቀደስ) ካገለገልን በኋላ፣ እራሳችንን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ማጠብና መቀደስ አለብን፡፡ «ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ» (1ኛ ቆሮ. 9÷27)፡፡
- ቁ. 29 «... በዚህ ቀን ትነጹ ዘንድ ማስተሰርያ ይሆንላችኋልና... <u>ራሳችሁን አስጨንቋት</u>»
- የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ከልብ በሆነ የኃጢአት ጸጸት (ንሥሐ) በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡበት ቀን ነው፡፡
- ቁ. 31 «... <u>ራሳችሁንም ታዋርዳላችሁ</u>፡፡»
- ቁ. 30 «... በእግዚአብሔር ፊት <u>ከኃጢአታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ</u>፡፡»

ቁ. 34 «ይህም አንድ ጊዜ በዓመት ለእስራኤል ልጆች ስለ ኃጢአታቸው ሁሉ ያስተሰርይ ዘንድ የዘላለም ሥርዓት ይሁንላችሁ፡፡»
በተጨማሪ ዘሌ 23፣26-32- ስለ ማስተሰሪያ ቀን ይናገራል፡፡

<u>ስለ መሠዊያው</u>፡ -(ምዕ. 17)

እስራኤላውያን ወይም በመካከላቸው የሚኖሩ እንግዶች በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ባለው መሠዊያ ላይ በስተቀር በየትም ሥፍራ መሥዋዕት ማቅረብ አይችሉም፡፡
ቁ. 4 «በእግዚአብሔር ማደሪያ ፊት ለእግዚአብሔር ቁርባን ያቀርብ ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ባያመጣው ደሙ በዚያ ሰው ላይ ይቆጠርበታል፡፡ ደም አፍስሶአል፤ ያም ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ»፡፡ ይህ ሐሳብ በቁ. 5 ና 9 ላይ ተደግሟል፡፡
ይህ የሚያመለክተው ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በስተቀር እውነተኛ መሠዊያ እንደሌለ ነው፡፡ ከኃጢአታችን ሁሉ መንጻትን ያገኘነው <u>በመስቀሉ</u> ላይ በፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው፡፡ ጳውሎስ፤ በገላ. 6፥14 «<u>ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ</u>፡፡» የሚለው ከመስቀሉ በስተቀር ሌላ መሠዊያ ስለሌለ ነው፡፡

## <u>የዘመኑ ሌሎች መሠዊያዎች</u>

የአሁኑ ዘመን የሃይማኖት ሰዎች (አንዳንድ ክርስቲያኖችም እንኳ) የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል በተለያዩ ነገሮች ሲተኩት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በራስ መተማመን (እምነት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ መሆኑ ቀርቶ በራስ እምነት ላይ ሲሆን)፥ በእምነት የተናገርከው ሁሉ ይሆንልሃል፥ መልካሙን ብቻ አስብ ይሆንልሃል አንተ ራስህ አምላክ ነህ፣ ወዘተ...»

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሐሳቦች ወይም ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ ትምህርት ላይ የተመሰረቱ ስለሆነ በሚሉት ነገር ውስጥ አንዳንድ እውነት የሚመስሉ ነገሮች ቢኖሩም ትምህርታቸውን መቀበል የለብንም፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል በሕይወታችን እንዲተኩ ስናደርግ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለይተው የሚያስቀሩን የሐሰት መሠዊያዎች ይሆናሉ፡፡

- መልካሙን ብቻ አስብ ምንም ጉዳት አይደርስብህም /Postive Thinking/ ያ መልካም ነው የምንለው ነገር እንደ

እግዚአብሔር ቃል እስከሆነ ድረስ መልካም የሆነውን ማሰብ አለብን፡፡ ነገር ግን የነገር ሁሉ መፍትሔ በአእምሮአችን መልካም የሆነውን ማሰብ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ማመን በመስቀሉ ፈንታ ሌላ መሠዊያ ተክተናል ማለት ነው፡፡ የእግዚብሔር ቃል ግን፤ «በእኔ ማለትም በሥጋዬ ምንም መልካም ነገር እንደሌለ አውቃለሁ» (ሮሜ7፣18) ነው የሚለን፡፡

- መልካም የሆነውን ነገር ብቻ ተናገር፣ ይሆንልኛል በል፡ - ይሆንልሃል /Postive confession/፡፡ አዎን የእግዚአብሔር ቃል፡ - «ለጻድቁ መልካም ይሆንልሃል በሉት» ይለናል፤ ነገር ግን ይህንን አስተሳሰብ እንደ መመሪያ ወስደን የተናገርኩት መልካም ነገር ሁሉ ይሆንልኛል ማለት ራስን ትልቅ ጉዳት ላይ የሚጥል ትምህርት ነው (የመስቀሉን ሥፍራ ሲወስድ መርዝ ይሆንብናል)፡፡

ቃሉን በአፋቸው ብቻ ለሚናገሩ በሕይወታቸው ግን ለሚያምጹ፣ የእግዚብሔር ቃል በመዝ. 49፣ (50)፥16-21 እንዲህ ይላል፤
«ኃጢአተኛውን ግን እግዚአብሔር አለው፣
ለምን አንተ ሕጌን ትናገራለህ?
ኪዳኔንም በአፍህ ለምን ትወስዳለህ?
አንተስ ተግሳጼን ጠላህ፣
ቃሎቼንም ወደ ኋላህ ጣልህ...» በሕይወታችን ቃሉን ካልኖርነው፥ በአፋችን ብቻ ብንናገረው ዋጋ አይኖረውም፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ የገባልንን የተስፋ ቃሎች ሁሉ ግን በልባችን ማመን፥ በአፋችንም መመስከር አለብን፡፡ «እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምሥክራቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት» (ራዕይ 12፥11)፡፡ ይህም ሆኖ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች በአፋችን ስላነበነብን ብቻ የተስፋውን ቃሎች እናገኛለን ማለት አይደለም፡፡ ጤናማ በሆነ መንገድ ግን የተስፋችንን ምሥክርነት መጠበቅ አለብን፡፡ «የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንጻይነቃነቅ የተስፋችንን ምሥክርነት እንጠብቅ» (ዕብ. 10፥23)፡፡ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል አጣመው ስለተጠቀሙ እኛ ያንኑ ቃል አቃንተን መጠቀም አንችልም ማለት አይደለም፡፡ «ያንን ቃል የሚጠቅስ ሰው ሁሉ ከዚያ የስህተት ትምህርት ጋር የተያያዘ ነው» ማለት በተቃራኒው አቅጣጫ አክራሪ መሆን ነው፡፡ ይልቁንስ፣ ጤናማ ባልሆነ መንገድ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ጥቅሶች አቃንተን በመጠቀም ጥቅሶቹን ከስህተት ትምህርት ምርኮኛነት መዋጀት አለብን፡፡

- ስለ ራስህ መልካም አመለካከት ይኑርህ፤ ሁሉ ነገር ይስተካከላል /Self-esteem/፡፡ ስለ ራሳችን መልካም አመለካከት ሊኖረን ይገባል፤ ነገር ግን በህይወታችን ያለውን ኃጢአት ደግሞ አስተውሎ እንደ ኢሳይያስ፡- «እኔ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ... ጠፍቻለሁኝና ወዮልኝ!» የሚልም ሕይወት ያስፈልጋናል (ኢሳ. 6÷4)፡፡
- አንተ ራስህ ትንሽ አምላክ ስለሆንክ÷ የአምላክነት እምቅ-ኃይል /Potential/ በውስጥህ እንዳለ ተረድተህ የአምላክነ ት ባህሪህን አሳድገው፡፡ ይህ ትምህርት ከሌሎቹ የስህተት ትምህርቶች ሁሉ የበለጠ አደገኛ የስህተት ትምህርት ነው፡፡ እንደውም÷ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጀመሪያ ተጠቅሶ የምናየው ሰይጣን ሔዋንን ያሳተበት የሐሰት ትምህርት ይሄ ነው፡፡ «እባብም ለሴቲቱ አላት፣ ሞትን አትሞቱም፣ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን አይኖቻችሁ እንዲከፈቱ <u>እንደ እግዘአብሔርም</u> መልካምንና ክፉን የምታወቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ» (ዘፍ. 3÷4-5)፡፡ ከጅምሩ፣ የሰይጣን ሽንገላና የሰው አወዳደቅ «<u>እንደ እግዚአብሔር</u> ለመሆን ከመፈለግ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የተቀባ ኪሩብ የነበረው ሰይጣንም ራሱ የወደቀው «<u>እንደ እግዚአብሔር</u>» ለመሆን በመፈለጉ እንደሆነ በኢሳ. 14÷12-15 እናያለን፡፡

ይህ የስህተት ትምህርት በዓለም ውስጥ «የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ» /The New Age Movement/ በመባል ሲታወቅ፤ በክርስትናው ዓለምም በተለያየ መንገድ ሥርጎ እየገባ ነው ይህንን የስህተት ትምህርት በክርስትና ስም አጥምቀውና ክርስትና አስነስተው «እኛ ትናንሽ ክርስቶሶች ነን» «እኛ ትናንሽ አምላኮች ነን» የሚሉ የሐሰት አስተማሪዎች በየቦታው ይታያሉ፡፡

ለእነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠው መልስ፣ «... ልብህ ኮርቷል፣ አንተም፤ <u>እኔ አምላክ ነኝ</u>፣ ... ብለሃል፣ ነገር ግን <u>ልብህን እንደ እግዚአብሔር ልብ ብታደርግም አንተ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም፡፡ ... በውኑ በገዳይህ ፊት÷ እኔ አምላክ ነኝ ትላለህን</u>? ነገር ግን <u>በገዳይህ እጅ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም</u>፡፡» (ሕዝ. 28÷ 2 እና 9) የሚል ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ትምህርቶች ሁሉ መልካምና የብርሃን መልአክ መስለው ከመስቀሉ የሚያርቁን መርዘኛ ትምህርቶች ናቸው፡፡

<u>በምዕራፍ 17 የምናያቸው ተጨማሪ ሐሳቦች</u>

በዘሌ. 17፣10-14፤ ሕይወት ያለችው በደም ውስጥ እንደሆነ ይናገራል።

«ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያል።» ቁ. 11
«የሥጋ ሁሉ ሕይወቱና ደሙ አንድ ነውና።» ቁ. 14

ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ሲያፈስልን ሕይወቱን ለእኛ ማፍሰሱ ነበር።

በቁ. 16 «ልብሱንና ገላውን ባያጥብ ግን ኃጢአቱን ይሸከማል» ይላል። ንስሐ ያልገባንበትን ኃጢአት ሁሉ እንደ ተሸከምን እንኖራለን።
እግዚአብሔር ካላስተዋልነው የኃጢአት ሸክም ይጠብቀን።
ዳዊት፤ «ከተሠወረ ኃጢአት አንጻኝ» ያለው ለዚህ ነው።

<u>የዘሌዋውያን አንደኛው ክፍል በአጭሩ ይህንን ይመስላል</u>

1. መሥዋዕቶቹ (ምዕ. 1-7)
2. የካህናቱ መቀደስ (ከምዕ. 8-10)
3. የሕዝቡ መንጻት (ምዕ. 11-16)
4. መሠዊያው (ምዕ. 17)

## ፪. ተግባራዊ የሆኑ ኃላፊነቶች (ዘሌ. 18-27)

ክፍል አንድ የሚያተኩረው <u>በተለያዩ ሥርዓቶችና መሥዋዕቶች መቀደስ</u> ወይም መንጻት /Positional Sanctification/ ላይ ሲሆን፤ ክፍል ሁለት የሚያተኩረው <u>በተግባር መቀደስ</u> ወይም በዕለት ተዕለት ኑሮ መቀደስ /Practical Santification/ ላይ ነው።

1. <u>ለሕዝቡ የተሰጡ ትእዛዛት</u፡ - (ከዘሌ. 18-20)

ሀ. ምዕ. 18- <u>ስለተለያዩ ዓይነት የዝሙት ርኩሰቶች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው</u>።

በዚህ ክፍል የምናየው እግዚአብሔር÷ ቤተሰብና ኅብረተሰብ በቅድስና እንዲጠበቁ እንደሚፈልግ ነው። ትዳርንና ቤተሰብን የመሠረተ እግዚአብሔር ስለሆነ ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት በኅብረተሰቡ መካከል እንዳይኖር ያስጠነቅቃል።
ምዕ. 18፣22- በተጨማሪ ግብረ-ሰዶምን ያወግዛል።

«ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ ፀያፍ ነገር ነውና» ይህንን ትእዛዝ የሚተላለፍ ሰው የሚደርስበትን ቅጣት በምዕ. 20÷13 ይናገራል፤ «ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል ፈጽመው ይገደሉ።»

ለ. ምዕ. 19- ሁለገብ ወይም ጥቅል የሆኑ ማስጠንቀቂያዎች ለምሳሌ፡ - ቁ. 14፡ - «ደንቆሮውን አትስደብ፣ በዕውርም ፊት ዕንቅፋት አታድርግ» ይላል።

- ስድብ ኃጢአት የሚሆነው ተሰዳቢው ሰው ስለሰማ ወይም ስለተጐዳ አይደለም። በመጀመሪያ የምንበድለው እግዚአብሔርን ነው። «አንተን ብቻ በደልኩ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ» (መዝ. 51÷4)።

ደንቆሮው ስድባችንን ስላልሰማ ዕውሩ የምናደርግበትን ስላላየ አይደለም። እግዚአብሔር ለደንቆሮው ይሰማለታል፣ ለዕውሩም ያይለታል።

ቁ. 17-18 «ወንድምህን በልብህ አትጥላው፤ በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ ገሥጸው። አትበቀልም፣ በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ።» የልብ ጥላቻ ሲውል ሲያድር ወደ ቂም በቀል መለወጡ ስለማይቀር ከጅምሩ የልብን ቅሬታ በተግሳጽ መልክ መግለጽ መንፈሳዊ ጤንነትን መጠበቅ ነው።

ቁ. 31 «ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ»

ቁ. 32 «በሽበታሙ ፊት ተነሣ፣ ሽማግሌውንም አክብር።» ይህ የእኛም አገር መልካም ባህል ነው።

ሐ. ምዕ. 20፡ - በምዕ. 18 እና 19 ላይ የተሰጡትን ትእዛዛት ለሚተላለፍ ሰው የተሰጡ የቅጣት ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው።

የቅጣቶቹ ዓይነት፡ -

- በድንጋይ መወገር
- ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ መጥፋት
- በእሳት መቃጠል ናቸው።

የእነዚህ ቅጣቶች አሠቃቂነት የሚያሳየው እግዚአብሔር ቅጣቱ በሚተላለፍባቸው ግለሰቦች ላይ ያለውን ጭካኔ ሳይሆን እግዚአብሔር ከግለሰቦቹ ይልቅ የኅብረተሰቡን ደኅንነት መጠበቅ እንደሚፈልግ ነው። አንድ ካንሰር በአካል ውስጥ ካለ ካንሰሩ

አካሉን በሙሉ እስከሚገድለው ድረስ አይጠበቅም፤ ነገር ግን ካንሰሩ ተቆርጦ መውጣት አለበት፡፡

2. <u>*ለካህናቱ የተሰጡ ትእዛዛት*</u>፡ - ከምዕ. 21-22

<u>*ይህ ክፍል በሦስት ይከፈላል*</u>፡ -

ሀ. ማድረግ የሌለባቸውን
ለ. መሆን የሌለባቸውን (ነውረኛና ርኩስ)
ሐ. ማሳረግ(መሥዋት) የሌለባቸውን ነገሮች ሲገልጽላቸው ነው፡ ፡

ሀ. ካህናቱ ማድረግ የሌለባቸው ነገሮች (ምዕ. 21፥1-15)

ይህ ክፍል ከምዕ. 18-20 በአጠቃላይ ለእስራኤላውያን ከተሰጠው ትእዛዝ በተጨማሪ ካህናቱ የበለጠ ቅድስና ስለሚጠበቅባቸው ለሌላው ተራ ሕዝብ የተፈቀዱ ለካህናቱ ግን ያልተፈቀዱ ነገሮችን ይዘረዝራል፡፡

ከእነዚህ ትእዛዞች መካከል፤

- ከቅርብ ቤተሰቡ በስተቀር አንድ ሰው ሲሞት ራሱን ማጐሳቆል አልተፈቀደለትም (ምዕ. 21፥1-6)
- ካህኑ ማንንም ሴት (እስራኤላዊ ስለሆነች ብቻ) ማግባት አይችልም (ምዕ. 21፥7-9)፡፡
- በይበልጥ ደግሞ ሊቀካህኑ በእናቱና በአባቱ ሞት እንኳን ራሱን እንዲያጐሳቁል አልተፈቀደለትም (ምዕ. 21፥10-12)፡፡
- ሊቀ ካህኑ ማግባት የተፈቀደለት ድንግሊቱን ብቻ ነው (ምዕ. 21፣13-15)፡፡

ለ. ከአሮን ዘር (ከካህናት) ነውር ያለበት ለእግዚአብሔር ቁርባን (መሥዋዕት) ማቅረብ እንደማይችል (ምዕ.21፡16-ምዕ. 22፣16) (ነውር ሲል በአካል ላይ ያለ ጉድለት ማለቱ ነው)፡፡

- በአዲስ ኪዳንም አማኝ ሁሉ የክህነት መብት ቢኖረውም በአገልግሎት አንጻር ግን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ የሚችል በመንፈሳዊ ሕይወቱ ነውር የሌለበት ሰው ብቻ ነው፡፡

- ነውረኛ ቢሆንም (የባህሪ ጉድለት ቢኖርበትም) እንኳ ቅዱሱን የአምላኩን እንጀራ ግን መብላት ይችላል (ምዕ. 21፣22-24)። ከእግዚአብሔር አገልግሎት ቢገለሉም ከእግዚአብሔር በረከት ወይም ጸጋ (ቅዱስ እንጀራ) ግን አልተገለሉም።
- ነገር ግን ለምጽ ወይም ፈሳሽ ነገር በሰውነቱ ላይ ያለበት፣ ወይም በማናቸውም ነገር የረከሰ የካህን ዘር እስከሚነጻ ድረስ መሥዋዕት አለማቅረብ (አለማገልገል) ብቻ ሳይሆን የተቀደሰውን እንጀራም መብላት አይችልም (ምዕ. 22፡1-16)። ይህ የሚያመለክተው የባህሪ ጉድለትን (ድካምን) ብቻ ሳይሆን አውቀን የምናደርገውን የአመጽ ኃጢአት ጭምር ነው። በኃጢአት ውስጥ ካለን የእግዚአብሔር ደስታ፥ ሰላምና ጸጋ እንኳን ይርቀናል።

ሐ. ማቅረብ ያለባቸው መሥዋዕት ነውር የሌለበት መሆን አለበት (ምዕ. 22፣17-33)

ቁ. 22 «ዕውር ወይም ሰባራ ወይም ጉንድሽ ወይም የሚመግል ቁስል ያለበት ወይም እከካም ወይም ቋቁቻም ቢሆን እነዚህን ለእሳት ቁርባን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር አታሳርጉ።»
የእነርሱ ነውረኛና ርኩስ አለመሆን ብቻ ሳይሆን የሚያቀርቡትም መሥዋዕት ነውረኛና ርኩስ መሆን የለበትም።

- እግዚአብሔር የሚያየው ወደ ሕይወታችንም ወደ መሥዋዕታችንም ነውና።

ዘፍ. 4፥4 «... እግዚአብሔር <u>ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ</u> ተመለከተ <u>ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ</u> ግን አልተመለከተም።» እኛስ አምላካችንን እንደሚገባ እንዳናገለግልና ለእርሱ መሥዋዕት እንዳናቀርብ የሚያደርገን ነውር ምንድነው? ከበረከቱስ (ከቅዱስ እንጀራው) እንዳንካፈል የሚያደርገን ርኩሰት ምንድነው? የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደምና የመንፈስ ቅዱስ እሳት ሊያስወግደው የማይችለው ነውርና ርኩሰት የለም። «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» (1ኛ ዮሐ 1፥7)።

## 3. <u>ስለ በዓላት የተሰጡ ትእዛዛት</u> --( ምዕ. 23)

እነዚህ በዓላት በየሳምንቱ ከሚመጣው የሰንበት በዓል የተለዩ በዓላት ናቸው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ 5 ዓመታዊ በዓላት አሉ::

ሀ. ፋሲካና የቂጣ በዓል (ቁ. 5-14)

ለ. በዓለ ሃምሣ (ቁ. 15-22)

ሐ. የመለከት ድምጽ በዓል (ቁ. 23-25)

መ. የማስተሰርያ ቀን በዓል (ቁ. 26-32)

ሠ. የዳስ በዓል (ቁ. 33-44)

ከእነዚህ ከአምስቱ ዓመታዊ በዓላት ውስጥ የሦስቱ ዓመታዊ በዓላት ብቻ ሳይሆኑ የደስታና ምግብ የሚበላባቸው (የፌስታ) በዓላት ናቸው:: በዘጸ. 23፣14-17 እና ዘዳ. 16፣16 ላይ «በዓመት ሦስት ጊዜ በዓል ታደርግልኛለህ» የሚለው እነዚህን የፌስታ በዓላት ማለቱ ነው::

እነዚህ ሦስቱ የፌስታ (የደስታና የግብዣ) በዓላት

1. የፋሲካ በዓል (የቂጣ በዓል)
2. በዓለ ኀምሣ (የጴንጤቆስጤ በዓል) - የመከር በዓል
3. የዳስ በዓል፡ -(የመክተቻው በዓል) ናቸው::

ሀ. የፋሲካ የቂጣ በዓል (ምዕ. 23÷5-14)

ይህ በዓል እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበትን ቀን ምክንያት በማድረግ የሚደረግ ዓመታዊ በዓል ነው:: የሞት መልአክ የግብፃውያንን በኵር ሁሉ ባጠፋበት ምሽት እስራኤላውያን በታዘዙት መሠረት የፋሲካውን ጠቦት አርደው ደሙን በቤታቸው መቃንና ጉበን ላይ ስለቀቡት የሞት መልአክ ሳይነካቸው በማለፉ የፋሲካ በዓል ተባለ (ዘጸ. 12÷1-20)::

ይህ በዓል የሚጀምረው በመጀመሪያው ወር በአስራ አራተኛው ቀን ማታ ሲሆን እስከ ሃያ አንደኛው ቀን ድረስ (ለ7 ቀናት) የቂጣ እንጀራ ( እርሾ የሌለበት) በመብላት የቂጣ በዓል ይሆንላቸዋል::

የፋሲካው ጠቦት የታረደው በ14ኛው ቀን ማታ ሲሆን፤ ከግብጽ የወጡት በ15ኛው ቀን ነበር::

በእነዚህ በሰባት ቀናት በየቀኑ ለእግዚአብሔር የእሳት ቁርባን ያቀርባሉ። በመጀመሪያውና በሰባተኛው ቀን ምንም ሥራ የማይሠሩበት የተቀደሱ ቀናት ይሆንላቸዋል።

በሰባተኛው ቀን ሰንበት ማግሥት ካጨዱት መከር የበኵራት ነዶ ወደ ካህኑ ያቀርባሉ (ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ) ዘሌ. 23፥10-11

ይህ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ደሙን እንዳፈሰሰልን የሚያመለክት በዓል ነው። «... <u>ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና</u>»( 1ኛ ቆሮ. 5፥7)። ኢየሱስ የተሰቀለው (ደሙን ያፈሰሰልን) በፋሲካ ጊዜ ነው( ዮሐ. 18፥28)።

ለ. <u>የጴንጤቆስጤ (በዓለ ኀምሣ) በዓል</u>። (ምዕ. 23፣15-22)

ከፋሲካና ከቂጣ በዓል 50 ቀናት በኋላ የሚውል በዓል ነው። «እስከ ሰባተኛ ሰንበት ማግስት ድረስ አምሳ ቀን ቁጠሩ አዲሱንም የእህል ቁርባን ወደ እግዚአብሔር አቅርቡ» (ቁ. 16)። ይህ በዓል በአንዳንድ ቦታ የመከር (የስንዴ መከር) በዓል ይባላል( ዘጸ. 23፥16፤ 34፥22)።

በቂጣው በዓል መጨረሻ ላይ የመከር ነዶ ለመወዝወዝ ቁርባን እንደሚያቀርቡ በበዓለ ኀምሣ በዓልም ከስንዴው መከር ለእግዚአብሔር የእህል ቁርባን ያቀርባሉ።

ይህ የበዓለ ኀምሣ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ከተነሣ ከኀምሳ ቀን በኋላ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ዕለት እንደሆነ በሐዋ. 2 ላይ እናነባለን።

በቂጣ በዓል ጊዜ የሚበላው ቂጣ እርሾ የሌለበት ነው( ዘጸ. 12፥15) በበዓለ ኀምሣ የሚበላው ግን በእርሾ የሚጋገር ነው( ዘሌ. 23፥17)።

የዚህ ምሳሌነት በፋሲካ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ፋሲካችን ሆኖ ለእኛ በመታረድ የዓለምን ኃጢአት ሁሉ ማስወገዱ ነው። «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ. 1፣29)።

እርሾ የኃጢአት ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን በፋሲካ ዕለት እርሾ የሌለበት ቂጣ ይበላሉ። ኃጢአታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም

ተወግዶአልና:: በበዓለ ኀምሳ ዕለት ግን እርሾ ያለበት እንጀራ የሚበሉት ምንም እንኳን ኃጢአታችንን በሙሉ የሚያስወግድ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ቢፈስም፣ በዕለታዊ ኑሮአችን ግን፡ -«ኃጢአት የለብንም ብንል ውሸተኞች ነን»( 1ኛ ዮሐ. 1÷8)::

1ኛ ዮሐ. 2፣1 «ልጆች ሆይ፣ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ:: ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::»

በበዓለ ኀምሣ የሚበላው እርሾ ያለበት እንጀራ፣ ኃጢአት ቢኖርብንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠበቃችን እንደሆነና እንዲሁም በምኅረቱ እንደተቀበለን የሚያመለክት ነው::

ሐ. <u>የመለከት ድምጽ በዓል</u> --( ምዕ. 23፣23-25)

ይህ የመለከት ድምጽ በዓልና የቀሩት ሁለት በዓላት ማለትም የማስተሰሪያው ቀን በዓልና የዳስ በዓል፡ - ሦስቱም በሰባተኛው ወር ውስጥ የሚከናወኑ ናቸው:: እነዚህ ሦስት በዓላት ከመጀመሪያዎቹ ሁለት በዓላት ራቅ ብለው የሚመጡ ናቸው:: የመለከት በዓል <u>በሰባተኛው ወር</u> <u>በመጀመሪያው ቀን</u> የሚውል በዓል ሲሆን ዓላማውም የሰንበት ወር(ሰባተኛው ወር-የዕረፍት ወር) መምጣቱን የሚያመለክት በዓል ነው::

ይህ የመለከት ድምጽ በዓል ሰባተኛ ወር ልዩ የዕረፍት ወር እንደሆነና የቀሩት ሁለት በዓላትም በዚሁ ወር እንደሚውሉ የሚያመለክት ነው::

ይህ የመለከት ድምጽ በዓል በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ልትነጠቅ ስትል ከሚሰማው መለከት ጋር ምሳሌነት አለው:: አማኞች ወደ ዕረፍታቸው የሚጠሩት በመለከት ድምጽ እንደሆነ በ1ኛ ቆሮ 15÷52 እናነባለን:: «እነሆ አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ፣ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋላኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፣ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን::» በተጨማሪም፣ ማቴ. 24÷31 «መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምጽ ጋር ይልካቸዋል ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ» ይላል::

መ. <u>የማስተሰርያ ቀን በዓል</u> --( ምዕ 23፣26-32)

ይህ በዓል በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን የሚውል ሲሆን ከበዓላቶቹ ሁሉ በትልቅ አክብሮትና ፍርሃት የሚከበር በዓል ነው። የእስራኤላውያን ኃጢአት በሙሉ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ አገር የሚሰረይበት፣ ሊቀካህኑም በዓመት አንድ ጊዜ በዚህች ዕለት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ የሚገባበት በዓል ነው( ዘሌ. 16ትን ተመልከት)። ሊቀ ካህኑ የእንስሳን ደም ይዞ ለራሱና ለሕዝቡ ኃጢአት በማስተሰረይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ እንደነበረ ሁሉ፤ እንዲሁም ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ራሱ ደም በሰማይ ወዳለችው ቅድስት እንደገባ እናነባለን (ዕብ. 9÷11-12፤ 24-26)። ሊቀ ካህኑ የስርየቱን ደም ይዞ ወደ ቅድስት ከገባ በኋላ እንደገና ተመልሶ እንደሚወጣ፤ ኢየሱስ ክርስቶስም ወደ ሰማያዊቱ ቅድስት እንደገባ እንዲሁ ከሰማይ ወጥቶ እንደሚመለስ ቃሉ ያስረዳናል። «.... ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል» (ዕብ. 9፣28)። እስራኤላውያን በዚህ ቀን በታላቅ ፍርሃትና ራስን በመመርመር ይቀርቡ እንደነበር ሁሉ÷ ይህ በዓል ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ ሁላችንም በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት የምንቀርብበትን ቀን ያሳስበናል።

ሠ. *የዳስ በዓል*፡ - (ምዕ. 23፣33-43)

ይህ በዓል በሰባተኛው ወር በ15ኛው ቀን የሚጀመር በዓል ነው (ቁ.34)፡፡ በዓሉ ለሰባት ቀናት ይቆያል። በዘጸ. 23÷16፣ የመከተቻው በዓል» ተብሎ የተጠቀሰው ይኼው በዓል ነው። የዚህ በዓል ዓላማ፤ እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በኋላ በዳስ ውስጥ እንደነበሩ የሚያስታውስ በዓል ነው። «ሰባት ቀን በዳስ ውስጥ ትቀመጣላችሁ፤ ከግብጽ ምድር ባወጣኋችሁ ጊዜ የእስራኤልን ልጆች በዳስ ውስጥ እንዳስቀመጥኋቸው የልጅ ልጆቻችሁ ያውቁ ዘንድ...» (ቁ.42)።

ይህ በዓል ከበዓላቶቹ ሁሉ ይልቅ «የደስታ በዓል» ነው (ዘሌ. 23÷40)። ይህ በዓል የበዓላቶቹ ሁሉ መጨረሻ ሲሆን የዓመቱ መከር የሚከተትበትም በዓል ነው። የመከተቻ በዓል የተባለውም ለዚህ ነው። ይህ በዓል የመጨረሻው በዓልና የታላቅ ደስታ በዓል የተባለውም ለዚህ ነው። ይህ በዓል የመጨረሻው በዓልና የታላቅ ደስታ በዓል እንደመሆኑ መጠን በዘመን ፍጻሜ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ለዘላለም በደስታ እንደምንኖር ያሳስበናል።

__የአምስቱ በዓላት ቅደም ተከተል፤__







ከላይ የተጠቀሱት 5 በዓላት በሙሉ ሁለት ተመሳሳይነት አላቸው:-

1. ሁሉም የዕረፍት ጊዜ ናቸው -ሥራ አይሰራባቸውም
2. የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚቀርብባቸው በዓላት ናቸው።

በመካከላቸው ጐልተው የሚታዩ ልዩነቶችም አሉ። ለምሳሌ: - የማስተሰሪያው ቀን በዓል ሰዎች ራሳቸውን የሚያስጨንቁበት የሚያዋርዱበትና ንሥሐ የሚገቡበት ዕለት ነው።

የዳስ በዓል ግን በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚሰኙበት ሳምንት (ሰባት ቀናት) ነው (ዘሌ. 23÷40)።

በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን በማስተሰሪያው ቀን ራሳቸውን ያስጨንቃሉ፣ ራሳቸውን ያዋርዳሉ (በእግዚአብሔር ፊት) በ15ተኛው ቀን ግን (በዳስ በዓል) በእግዚአብሔር ፊት ለ7ቀናት ደስ ይላቸዋል። ከዚህ የምንማረው፤ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን አዋርደን ንሥሐ ሳንገባ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ልንሰኝ እንደማንችል ነው። «የሚያዝኑ ብጹዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና» (ማቴ. 5÷4)።

## ምዕራፍ 24 - እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው አንዳንድ ማሳሰቢያዎች

ከቁ. 1-9፤ ስለመቅረዙና ስለ ኅብስት ገበታው።

«መብራቶቹን ሁልጊዜ እንድታበራበት ለመብራት ጥሩ ተወቅጦ የተጠለለ የወይራ ዘይት ያመጡልህ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው» (ቁ.2)። ብርሃናችን ሁልጊዜ መብራት እንዳለበትና ማሰሮአችን በዘይት መሞላት እንዳለበት ያሳስበናል (ሉቃ. 12፥35)፣ (ማቴ. 25፥1-13)።

ከቁ. 10-23፣ የእግዚአብሔርን ስም ስለሰደበ አንድ ግብጻዊ ሰው።

ይህ ሰው አባቱ ግብጻዊ እናቱ ግን እስራኤላዊት ነበረች። ከጅምሩም የተቃወሰ ጋብቻ ነበረ ማለት ነው። «ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ አትጠመዱ» (2ቆሮ. 6፥14)።

«... የእግዚአብሔርን ስም ሰደበ፣ አቃለለውም፤ ወደ ሙሴም አመጡለት። ... ከእግዚአብሔርም አፍ ስለ እርሱ ፍርድ እስኪወጣላቸው ድረስ በግዞት አኖሩት» (ቁ. 11-12)። እግዚአብሔር ለሙሴም እንኳን ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ እንዳልነገረው እናያለን። አንዳንድ ጊዜ ተጽፎ ከተሰጠን ውጭ የሆነ ሁኔታ ሊያጋጥመን እንደሚችልና በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ጊዜ መውሰድ እንዳለብን ያሳስበናል።

እግዚአብሔርም ይህ ሰው በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት ፍርድ ያስተላልፋል። ፍርዱ ለዚህ ሰው ብቻ ሳይሆን «ማናቸውም ሰው አምላኩን ቢሰድብ ኃጢአቱን ይሸከማል። የእግዚአብሔርን ስም የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል» (ቁ. 15-16) የሚል ትእዛዝ ይወጣል።»

ጥርስ በጥርስ ፈንታ ዐይን በዐይን ፈንታ የሚለው የኦሪት ሕግ የተሰጠው በዚህ ምዕራፍ ነው ቁ. 19-20።

## 3. ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ የሚፈጽሙት ትእዛዛት (ምዕ. 25-27)

ከአምስቱ ዓመታዊ በዓላት ሌላ ሁለት ዓመታዊ ያልሆኑ በዓላት እንዳሉ በምዕ. 25 እናነባለን።

<u>የሰባተኛው የሰንበት ዓመት በዓል</u>፡ - በየሰባተኛው ዓመት የዕረፍት ዓመት ይሆንላቸዋል። አያርሱም፣ አይዘሩም፣ አያጭዱም። ምድሪቱ ሳትቀር ታርፋለች።

<u>የኢዮቤልዩ ዐመት በዓል</u> (በየ50ኛው ዓመት የሚፈጸም)። ይህ በዓል የዕረፍት ዓመት ሆኖ በተጨማሪ ሰው ሁሉ ከዕዳ፣ ከባርነት ወዘተ... ነጻ የሚሆንበትና ርስትም ሁሉ ለባለቤቱ የሚመለስበት በዓል ነው።

ሀ. ስለ ሰንበት ዓመትና ኢዮቤልዩ የተሰጠ ትእዛዝ (ምዕ. 25)

ለ. የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም የሚያስገኘው በረከትና ትእዛዙን መተላለፍ የሚያመጣው ቅጣትና መቅሠፍት (ምዕ. 26)

ሐ.( በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር የሚሰጡ (የሚቀደሱ) ነገሮች፡፡ (ምዕ. 27)

ሀ. <u>የሰንበት (ሰባተኛው) ዓመትና፣</u>

<u>የኢዮቤልዩ (50ኛው) ዓመት</u> (ምዕ. 25)

«እኔ ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ <u>ምድሪቱ ለእግዚአብሔር ሰንበት ታድርግ</u>... በሰባተኛው ዓመት ግን <u>ለምድሪቱ የዕረፍት ሰንበት ለእግዚአብሔር ሰንበት</u> ትሁን» (ዘሌ. 25÷10)፡፡

በዚህ ክፍል የምናየው እግዚአብሔር ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለምድሪቱ እንኳ እንደሚያስብ ነው፡፡ ምድሪቱ እንኳ ሳትቀር እፎይ ማለት እንዳለባት እናነባለን፡፡ በሮሜ8፡19-22 በምናይበት ጊዜ ፍጥረት ሁሉ ከጥፋት ባርነት ነፃ ለመሆን እንደሚቃትት እናያለን፡፡ በኤር 12፡4 ደግሞ ተመሳሳይ ቃል እናነባለን፡፡

«ምድሪቱ የምታለቅሰው የአገሩስ ሣር ሁሉ የሚደርቀው እስከመቼ ነው? ... ስለ ክፋታቸው እንስሶችና ወፎች ጠፍተዋል፡፡» በዘመናችን የምናየውን የውሃና የአየሩን መበላሸት Air & Water pollution እንዲሁም የአፈሩንና የዛፎችን ማለቅና በበረሃ መወረስ Deforestation & Soil erosion ያሳያል፡፡

በግብርና ሳይንስ እንደተረጋገጠው፣ ይህ እግዚአብሔር ምድሪቱ እንድታርፍ የሰጠው ትእዛዝ ምድሪቱ የበለጠ ፍሬያማ እንድትሆን ያደርጋታል፡፡ የዚህ የሰባተኛው ዓመት ዕረፍት ዓላማ፤ አንድ ዓመት ሳትታረስና በውስጧ ያለው ንጥረ ነገር የበለጠ ሳይሟጠጥ እፎይ ስትል ባለፉት ስድስት ዓመታት የሰጠችውን ንጥረ ነገር እንደገና ለማግኘት ጊዜ ታገኛለች፡፡

ይህንን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከፈጸሙ ምድሪቱ (በ6ኛው ዓመት የሦስት ዓመት ፍሬ ለ6ተኛው፣ ለ7ተኛውና ለ8ተኛው ዓመት) ታፈራለች (ዘሌ. 25፡20-22)።

በዚህ ምዕራፍ የምናየው ሌላ በዓል ደግሞ የ50ኛው ዓመት ኢዮቤልዩ ነው። ሰባት የሰባት ዓመታት ሰንበቶች (49 ዓመታት) ካለፉ በኋላ ኀምሳኛው ዓመት በአገሪቱ በሙሉ ነጻነት የሚታወጅበት ዓመት ነው።

«ኀምሳኛውን ዓመት ትቀድሳላችሁ በምድሪቱም ለሚኖሩባት ሁሉ <u>ነጻነትን ታውጃላችሁ</u> እርሱ ለእናንተ ኢዮቤልዩ ነው። ሰው ሁሉ ወደ ርስቱና ወደ ወገኑ ይመለስ» (ዘሌ. 25÷10)

- 49ኛውና 50ኛው ዓመታት የዕረፍት ዓመታት ናቸው። (ቁ. 11) አንድ አይሁዳዊ ርስቱን ለሌላ ሰው ቢሸጥ ወይም ራሱን እንደ ባሪያ አድርጎ ቢያስገዛ በኢዮቤልዩ ዓመት ርስቱ ይመለስለታል እርሱም ነጻ ይወጣል።

  እግዚአብሔር የነጻነት አምላክ እንደሆነ ሁሉ፤ ሕዝቡም የነጻነት ሕዝብ እንደሆነ የሚያሳይ በዓል ነው። አንድ አይሁዳዊ በተለያዩ ምክንያቶች ርስቱ ቢወሰድ ወይም ባሪያ ቢሆን በሕይወት ዘመኑ ነጻ የመሆን ተስፋ አለው ማለት ነው። ይህ በዓል በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያገኘውን ነጻነት የሚያመለክተው ነው።

  ገላ. 5፣1 «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ፥ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ»
  «የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ።» (1ኛ ቆሮ 3÷17)።

ይህ በዓል የሚታወጀው በ49ኛው ዓመት በማስተሰሪያ ቀን (በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን) ነው (ዘሌ. 25÷8-10)። በዚህ እስራኤላውያን ሁሉ ንስሐ በሚገቡበት የስርየት ዕለት ወንድሞቻቸውን ሁሉ ነጻ ለማውጣት (ርስታቸውን ገዝተው ከነበረ ወይም እንደ ምንደኛ ይሰሩላቸው) ከነበረ ፈቃደኛ መሆን ነበረባቸው።

በተጨማሪ፤ በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር «ምድር የእኔ ናት ምድርን ለዘላለም አትሸጡ (ቁ. 23) ሲል እናነባለን። ምድር ሁሉ የእርሱ ስለሆነች ነው በኢዮቤልዩ ዓመት ከሌላው የወሰዳችሁት (የገዛችሁት) ርስት ካለ ለባለርስቱ መልሱ የሚላቸው።

## ለ. የመታዘዝና የአለመታዘዝ ውጤት ዘሌ. 26

ይህ ምዕራፍ ከዘዳግም 28 ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ዘዳግም የሕጉ በድጋሚ ለአዲሱ ትውልድ መሰጠት እንደመሆኑ መጠን የዚህ ምዕራፍ ማስጠንቀቂያ በዘዳግም 28 ሲደገም እናያለን፡፡

### 1. ትእዛዙን የመጠበቅ በረከት (ዘሌ. 26፥3-13)

#### የኢኮኖሚ በረከት

የዝናብ በረከት - እህልና ፍራፍሬ ቁ. 4-5

#### የኅብረተሰብ በረከት

ሰላም- ከጦርነት ከአራዊት ቁ. 6
በጠላት ላይ ድል (ቁ. 7-8)

#### መንፈሳዊ በረከት

የእግዚአብሔር ሞገስና መገኘት (ቁ. 9-13)

### 2. ትእዛዙን በመተላለፍ የሚመጣ እርግማን -- ዘሌ. 26፥14-39

#### የግል ሕይወት እርግማን

ፍርሃትና የጤንነት ቀውስ ቁ. 16

#### የኅብረተሰብ እርግማን

በጠላት መሸነፍ - «የሚጠሏችሁ ይገዙአችኋል ቁ. 17

#### የኢኮኖሚ እርግማን

ሰማይ እንደ ብረት ምድርም እንደ ናስ ትሆናለች (ቁ. 18-20)
የምድር አራዊት ልጆቻችሁን ይነጥቃሉ (ቁ. 21-22)
ሰይፍና ቸነፈር (ቁ. 23-26)
የወንዶችና የሴቶች ልጆቻችሁን ሥጋ ትበላላችሁ (ቁ. 29)

## <u>መንፈሳዊ እርግማን</u>

መቅደሶቻችሁን አፈርሳለሁ (ቁ. 31)

በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ (ቁ. 33-39)

በዚህ ክፍል የምናየው ንሥሐ ካልገባን የእግዚአብሔር ቁጣ እየጨመረ እንደሚሄድ ነው። እግዚአብሔር እልህን የሚያስጨርስ አምላክ ነው።

- እግዚአብሔር በመጀመሪያ ያስተምረናል፣ ይመክረናል፣ ያስጠነቅቀናል። ትምህርቱን ምክሩንና ማስጠንቀቂያውን የሚሰጠን ገና ስህተት ውስጥ ሳንገባ ነው። ቃየን ወንድሙን አቤልን ከመግደሉ በፊት መክሮ (አስጠንቅቆት) እንደነበር በዘፍ. 4÷6-7 እንመለከታለን። «እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፤ ለምን ተናደድክ» ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፤ አንተ ግን በእርስዋ ንገስባት።»

- ትእዛዙን በምንተላለፍበት ጊዜ፤

  ሀ. በመጀመሪያ ይገሥጸናል <u>ተግሣጽ</u>
  ለ. ተግሣጹን ሰምተን ካልተመለስን ይቀጣናል - <u>ቅጣት</u>
  ሐ. በአመጽ ከቀጠልን ቁጣው በእኛ ይነዳል - <u>ቁጣ</u>

አንድ ሰው በአመጽ እየቀጠለ ከሄደ የእግዚአብሔርም ቁጣ እየጨመረ እንደሚሄድ ከዘሌዋውያን 26 እንማራለን።

ቁ. 18 «እስከዚህም ድረስ ባትሰሙኝ ስለ ኃጢአታችሁ በቅጣታችሁ ላይ <u>ሰባት እጥፍ</u> እጨምራለሁ» (7 እጥፍ)

ቁ. 21 «በእንቢተኝነት ብትሄዱብኝ ባትሰሙኝም ... በመቅሠፍት ላይ <u>ሰባት እጥፍ</u> እጨምራለሁ» (7×7 እጥፍ)

ቁ. 23 «እስከዚህም ድረስ ባትቀጡ ... <u>ሰባት እጥፍ</u> እመታችኋለሁ» (7×7×7 እጥፍ)

ቁ. 27 «እስከዚህም ድረስ ባትሰሙኝ ... እኔ ደግሞ በቁጣ እሄድባችኋለሁ... <u>ሰባት እጥፍ</u> እቀጣችኋለሁ» (7×7×7×7 እጥፍ)

## <u>የእግዚአብሔር ምሕረት</u>

እግዚአብሔር ያንን ሁሉ ቅጣትና መቅሠፍት ካወረደባቸው በኋላ በንስሐ ወደ እርሱ ቢመለሱ ይቅር እንደሚላቸው ይናገራል፡፡ «ነገር ግን በዚያን ጊዜ ያልተገረዘው <u>ልባቸው ቢዋረድ የኃጢአታቸውንም ቅጣት ቢቀበሉ</u> ... ለአብርሃም የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ ምድሪቱንም አስባለሁ» (ዘሌ. 26፡ 41-42) ፡፡

ሐ. <u>የፈቃደኝነት (ስጦታ) ስእለት</u> (ምዕ. 27)

- ሰው <u>ሰውን</u> ለእግዚአብሔር ሊሰጥ ቢሳል፡ -(ቁ. 23)
  ልጁን ሊሆን ይችላል ባሪያውን ሊሆን ይችላል፡፡
- የሚያቀርበው መሥዋዕት <u>እንስሳ</u> ቢሆን (ቁ. 9)
- ሰውም <u>ቤቱን</u> ለእግዚአብሔር ቢቀድስ (ቁ. 14)
- ሰውም <u>ርስቱን</u> ለእግዚአብሔር ቢቀድስ (ቁ.16)

- እነዚህ ሁሉ፣ ከላይ የተዘረዘሩት አንድ ሰው በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር ሊሰጥ (ሊሳል) የሚችላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ለእኔ ነው ብሎ በሕጉ ወስጥ የተናገራቸው አስራትና በኩራትና በተጨዌ ሰው <u>በፈቃደኝነት</u> የሚሰጣቸው ስጦታዎች ናቸው (ዘሌ. 27፡30-32) ፡፡

የዘሌዋውያን መጽሐፍ እግዚአብሔር ከእስራኤላዊያን ጋር ሊኖረው ስለሚፈልገው ግንኙነት (ኅብረት) የሚገልጽ እንደመሆኑ መጠን የሚያልቀውም ሕዝቡ በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር በሚሰጡት ስጦታ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን የሚገባው ግንኙነት ከእግዚአብሔር መልካምን ነገር <u>በመቀበል ብቻ</u> ሳይሆን እኛም ለእግዚአብሔር <u>በፈቃዳችን የፍቅር ስጦታ</u> በመስጠት መሆን አለበት፡፡

# ምዕራፍ አራት፣ ጥያቄዎች

1. የአሪት ዘሌዋውያን ዋና መልእክት ምንድነው? የመጽሐፉ መሪ ጥቅስ ምንድነው?

2. የዘሌዋውያን መጽሐፍ የሚከፈልባቸው ሁለት ክፍሎች ምንድነው ናቸው?

3. አምስቱን የመሥዋዕት ዓይነቶች ከጠቀስክ በኋላ ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ ሆነው የሚቀርቡትን ለይ።

4. በኀጢአት መሥዋዕትና በበደል መሥዋዕት መካከል ያለውን ልዩነት ጥቀስ።

5. በብሉይ ኪዳን የነበሩ ካህናትና ሊቀ ካህን በአዲስ ኪዳን የማንና የማን ምሳሌ ናቸው?

6. ሙሴ፤ አሮንንና የአሮንን ልጆች ለክህነት ሲቀድሳቸው፤ ከሰውነታቸው ሦስት ቦታዎች ደም ያስነካ ነበረ፤ እነዚህን የሰውነት ክፍሎችና በደም የተነኩበት ትርጉም ምን እንደሆነ ግለጽ?

7. በእግዚአብሔር የተቀሰፉት ሁለቱ የአሮን ልጆች እነማን ናቸው? ለምንስ ተቀሰፉ? እኛስ ከዚህ የምንማረው ምንድነው?

8. በዘሌዋውያን 14 ላይ ስለ ለምጻም ሰው መንጻት ሥርዓት ሲናገር፤ ለምጻሙ የሚነጻባቸው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው? እነዚህ ሦስት ነገሮች በአዲስ ኪዳን ምን ምሳሌነት አላቸው?
9. በዘሌዋውያን ውስጥ የተጠቀሱትን አምስት የእስራኤላውያን ዓመታዊ በዓላት ከጠቀስክ በኋላ የሆኑበትን ምክንያት በአጭሩ ግለጽ።
10. ዓመታዊ በዓላት ባይሆኑም ከአምስቱ ዓመታዊ በዓላት በተጨማሪ የሚከበሩትን ሁለት ልዩ በዓላትና ምን የሚከናወንባቸው በዓላት እንደሆኑ ጥቀስ (የሰንበትን ቀን በዓል አይጨምርም)።